# አዲስ አበበ ዩኒቨርስቲ


## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ2014 ዓ ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ


በ

ተረፈ ኤርሰዶ


ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የስነሰብ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና

## ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር

## ትምህርት ክፍል ፣ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


### በ2014 ዓ ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ


**<u>በ</u>**

**ተረፈ ኤርሰዶ**

**<u>አማካሪ</u>**

**ደረጀ ገብሬ**



ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የስነሰብ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና

## ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር

## ትምህርት ክፍል ፣ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ2014 ዓ ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ

**በ**

**ተረፈ ኤርሰዶ**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

| ስም | ፊርማ |
|---|---|
| አማካሪ........................................... | ........................... |
| ፈታኝ............................................ | .......................... |
| ፈታኝ............................................ | .......................... |

**ጥቅምት 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ምስጋና

በመጀመሪያ ዛሬዬን ቀድሞ ላየ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ ይህ ጥናት አሁን የያዘውን ቅርጽና ይዘት እንዲያገኝ ርዕሱን ከማስተካከል ጀምሮ በያንዳንዱ ደረጃ የአሰራር አቅጣጫ በማሳየት፣ ስራዬን ባለመሰልቸት በማንበብ እርምትና ማስተካከያ ላደረጉልኝ አማካሪዬ አቶ ደረጀ ገብሬ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ውጤት ያለው እንዲሆን ፍላጎቴን ቀድሞ በማወቅ፣ የራሱም ራዕይ እንዲሳካ ጭምር በሀሳብም ሆነ በቁሳቁስ ለደገፈኝ ውድ ጓደኛዬ አቶ ጥላሁን በየነ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡

ለቤተሰቤ መዋል ያለበትን የክረምት ጊዜ ለትምህርቴ መድቤ ስማር የቤቱን ክፍተት ሙሉ በሙሉ በመሸፈን ድካሙን የቻለችውን ውድ ባለቤቴ ራሔል ኤርምያስን ረጅም ዕድሜ ከጤና ያብዛልሽ ከማለት ሌላ የለኝም፡፡ በተለይ አይዞህ በርታ ትችላለህ ብለው በማበረታታት ከጎኔ ለቆሙ ልጆቼ ቤተልሔም ተረፈ ፣ሩሃማ ተረፈ ፣ሮቤል ተረፈ፣ከኣብ ተረፈ፣ ኣሰንቻ ተረፈና አሚ ተረፈ እደጉ፣ አስተሳሰባችሁን አምላኬ ይባርክ ከማለት ሌላ የለኝም፡፡

በመጨረሻም ለጥናቱ መሳካት አስተዋጽኦ በማበርከት በቃለ መጠይቅ ለተሳተፉ የከምባታ ዞን ዱራሜ ከተማ ህዳሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ፈቅደው ለደረጉት ትብብር ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማረጋገጫ

“በ2014 ዓ ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስናጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በሌላ በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቤዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም…………………………..

ፊርማ………………………..

ቀን………………………….

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በ2014 ዓ ም በትምህርት ሚኒስቴር ታትመው በ2015 ዓ ም ለሙካራ በጥቂት የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የስርጭት ሽፋን ባገኙ የ9ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፍድራል ቋንቋ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍ መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ የሚል ነው።የጥናቱ ዓላማ ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ያለውን የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው።የጥናቱ ንድፍ መረጃዎቹ ከሰነድና ቃለ መጠይቅ የተገኙ እንደ መሆናቸው መጠን የመጣጣሙን ጥልቀትና አሳሳቢነት ማሳየትን ስለሚሻ ንድፉ ገላጭ የሚባለው ነው። የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው። ሰነድ ፍተሻ ዋና የመረጃ ምንጭ ሲሆን ቃለ መጠይቅ ደግሞ ደጋፊ ነው።ቃለመጠይቁ የተከናወነው ለሙከራ ትግበራ በተመረጠ ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንን በመጠቀም ነው።የመረጃ አተናተን ዘዴው አይነታዊ የሚባለው ነው።ምክንያቱም መረጃዎቹ አሃዝን መሰረት ያላደረጉ በመሆናቸው ነው። ጥናቱ አዎንታዊም አሉታዊም ውጤት አሳይቷል፡በአዎንታ በኩል ከይዘት ተገቢነት አንጻር ለአንቀጽና ለድርሰት ትምህርቶች የጎላ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል፡፡"መርሀ ትምህርት" መባል ያለበት በክፍሉ የመምህር መምሪያ መጽሀፍ ውስጥ "ስርዓተ ትምህርት" ተብሎ ተቀምጧል። "መርሀ ትምህርት"ተብሎ በባል ያለበት ነው።የጽህፈት ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ በመርሀ ትምህርቱ በክፍል አራት ተፈጥሯዊውን የቋንቋ ለመዳ ቅደም ተከተል ይዞ የተቀመጠ ቢሆንም በተማሪው መጽሐፍ በክፍል አምስት መቀመጡ ከተፈጥሯዊነትም ሆነ ከትምህርት መሳሪያዎቹ የይዘት ቅደም ተከተላዊ ተጣጣሚነት አንጻር ክፍተት ያሳየ ያለመጣጣም ነው።ከፍተኛ የአረዳድ ችግር የማስከተል አቅም ባይኖራቸውም መርሀ ትምህርቱ ድርሰት በሚል ርዕስ ሰጥቶ እያለ የተማሪው መጽሀፍ አንቀጽ ያላቸው፣የድርሰት አይነቱ ሳይለይ "ድርሰት ጻፉ" የሚሉ ትዕዛዞች፣የጽህፈቱን ደረጃ ሳይለዩ "ጻፉ" ወይም "በጽሁፍ ግለጹ" በሚል የቀረቡ መልመጃዎች በመምህራኑና በያዙት የሀሳብ ስፋት የሚወሰኑ ጽሁፎች ቢሆኑም አይነታቸው አንቀጽ፣ድርሰት…በሚል ተለይቶ አለመገለጽ የሚሉ ይገኙበታል።

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና ............................................................. I

ማረጋገጫ ............................................................. II

አጠቃሎ ............................................................. III

ማውጫ ............................................................. V

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ............................................................. 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............................................................. 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............................................................. 3

1.3 የጥናቱ አላማ ............................................................. 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ............................................................. 4

1.5 የጥናቱ ወሰን ............................................................. 5

1.6 የጥናቱ ውሱንነት............................................................. 5

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት ............................................................. 6

2.1 የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች ምንነት ............................................................. 6

2.1.1 የመርሀ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት ............................................................. 6

2.1.2. የቋንቋ መርሀ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ............................................................. 19

2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነትና አስፈላጊነት ......................... 10
2.2.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት ......................... 10
2.2.2 የቋንቋ መማሪያ መፍሐፍ አስፈላጊነት ......................... 11
2.3 የመርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍት ግንኙነት (ተጣጣሚነት)......................... 12
2.4 የቋንቋ ክሂሎችና የይዘት ምንነት ......................... 13
2.4.1 የቋንቋ ይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች ......................... 14
2.5 የጽህፈት ክሂል ምንነትና አስፈላጊነት......................... 14
2.5.1 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ......................... 16
2.5.2 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አላማ ......................... 17
2.5.3 የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ......................... 20
2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ......................... 20
ምዕራፍ ሦስት
የአጠናን ዘዴ ......................... 23
3.1 የጥናቱ ንድፍ ......................... 23
3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ......................... 23
3.3 መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ......................... 23
3.3.1 የሠነድ ምርመራ ......................... 24
3.3.2 ቃለመጠይቅ ......................... 24
3.3.3 የናሙና አመራረጥ ......................... 24
3.4 መረጃ የመተንተን ዘዴ ......................... ……………25

ምዕራፍ አራት


የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 27

4.1 የመረጃ ትንተና ........ 27

4.1.1 የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አጭር መግለጫ ........ 27

4.1.2 በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት አጠቃላይ ይዘቶች ትንተና ........ 27

4.1.3 የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ

የተጠቀሙ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ሥርጭት ........ 29

4.1.4 በ2014 ዓ.ም በተዘጋጀ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ

መጽሐፍ ውስጥ ለማስተማሪያነት የቀረቡ ይዘቶች ትንተና........ 34

4.1.5. የ2014 ዓ.ም ህትመት የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ

መጽሐፍ የጽህፈት ትምህርት ይዘት ትንተና ........ 35

4.1.6. የ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

የጽህፈት ክሂል ይዘት መልመጃዎች ለክፍሉ ከተዘጋጀው መርሀ

ትምህርት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ........ 39

4.2 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንታኔ ........ 43


ምዕራፍ አምስት


ማጠቃለያ የጥናቱ ግኝትና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 52

5.1 ማጠቃለያ ........ 52

5.2 የጥናቱ ግኝት........ 52

5.3 የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 54

ዋቤ መፃህፍት ........ 56

አባሪ 1. ........ 60

## የሠንጠረዥ ማውጫ


**ርዕስ** **ገጽ**

ሠንጠረዥ 1፡ ለ9ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ መርሀ ትምህርት
አጠቃላይ ይዘቶች ........ 25

ሠንጠረዥ 2፡ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሀ ትምህርት አጠቃላይ
ይዘቶች ሥርጭት ........ 28

ሠንጠረዥ 3፡ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ በየምዕራፉ
የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ........ 29

ሠንጠረዥ 4፡ የ 9ኛ ክፍል አማርኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ ያለው
የመጻፍ ክሂል ርዕሶች የሥርጭት ሽፋን ........ 30

ሠንጠረዥ 5፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለው የይዘት ሥርጭት ........ 33

ሠንጠረዥ 6፡ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ የቀረበው የመጻፍ
ክሂል ይዘት ሥርጭት ........ 36

ሠንጠረዥ 7፡ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የመጻፍ
ክሂል ይዘት የሥርጭት ሽፋን ........ 38

ሠንጠረዥ 8፡ የመጻፍ ክሂል ይዘት ሥርጭት የ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው
መጽሐፍና በመርሀ ትምህርት መካከል ያለው ተጣጥሞሽ ........ 62

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሚዘጋጁት መርሃ ትምህርትን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ክሂሎችን ለመጠቀም መርሃ ትምህርቱ የመነሻ ጽሁፍ ሆኖ ማገልገል እንደሚችል Harmar (1992) ይገልጻል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በስርዓተ ትምህርት የተደገፈ ዝግጅት ተደርጎለት እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሰጠት የጀመረው ከ1948 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ አለም (1992) ይገልጻሉ፡፡

አለም(1992) በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የተዘጋጁት የትምህርት መሳሪያዎች በዝግጅት ወቅት በሚከሰቱ ስህተቶች ምክንያት ችግሮች እንደሚስተዋሉባቸው ገልጸዋል፡፡ ምሁሩ የችግሩን ስፋት ገልጸው የትምህርት ባለሙያዎች የትምህርት መስጫ መሳሪያዎቹን በየጊዜው በመፈተሸ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ያሳስባሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የጽህፈት ክሂል የታለመለትን ግብ በሚጠበቀው ደረጃ ያልመታ እንደሆነ ባየ(1987)ና ተስፋዬ(1981) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን የመጻፍ ክሂል በተማሪዎች ዘንድ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ድረስ በጣም አስቸጋሪና ከስህተቶች ያልጸዳ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ባየ(1987)ና ተስፋዬ(1981)፣ የRichards(1974)ን ሀሳብ በሚያጎላ መልኩ "በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንኳን አብዛኞቹ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ በተማሩት መሰረት ጥሩ ጽሁፍ ሲጽፉ አይታይም፡፡ ቁጥራቸው ይህ ነው የማይባል በርካታ ተማሪዎች ለጽሁፍ ፍራቻና ጭንቀት ይታይባቸዋል" በማለት ገልጸዋል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ እየተማሩት ባለው ቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት በማዳበር እንዲግባቡ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የመማሪያ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለ ቋንቋ ትምህርት ሲነሳ ቁልፉን ቦታ የሚይዙት የመማሪያ መሳሪያዎች መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ጥናታቸውን ያደረጉ ተመራማሪዎች Grant(1987)፣ Cunningsworth (1995)እና Richards (2001) ገልጸዋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረጹት ዓባይት አላማዎች ውስጥ አንዱ አራቱን

የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት ሲሆን በተላይ በቋንቋ ክሂሎች አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠት እንዳለበት (Byme 1981፣107) ገልጸዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማዳበር የሚል ነው፡፡ ይህ  አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ ተደራጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ በትምህርት መሳሪያዎቹ ውስጥ በቀረበው የጽህፈት ክሂል ላይ ጥናት ማድረግና ለክሂሉ ማዳበሪያነት የቀረቡት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ  ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡

የመማሪያ መጽሀፍ የታላሚውን ተማሪ የዕውቀት አድማስ የሚያሳደግ፣ለመምህሩም ሆነ ለመማር ማስተማሩ ተግባር ቀልፍ መሳሪያ ነው፡፡ የመማር ማስተማር ስራ አሀዱ ተብሎ ሲጀመር የቋንቋ ትምህርቱን፣ መምህሩንና ተማሪውን በአንድነት የሚያስተሳስር መሳሪያ ይኸው የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ CunningsWorth (1997፣7) እንደገለጹት የመማሪያ መጽሃፍ የተማሪውን የመማር ልምድ የሚያዳብርና ተማሪውን ለትምህርት ሊያነሳሱ የሚችሉ የተለያዩ ምንባቦችን፣ የማስተዋል ጥያቄዎችን፣ የስነ-ልሳንና የስነ-ጽሁፍ ዕውቀቶችንና በዋነኛነት የቋንቋ ክሂሎችን አመጣጥኖ የያዘ መሳሪያ ነው፡፡ ይዘቶችን ለመተግበር በሚደረግ ሂደትም ተማሪውንና አስተማሪውን የሚያገናኝ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ስለዚህ የሚመረጡትና የተቀነባበሩት የቋንቋ ይዘቶች የሚከተሉትን ነጥቦች ሊያገናዝቡ ይገባል፡፡ የቋንቋ አላማ ሊያሳኩ የሚችሉ፣ የተማሪውን ዕውቀትና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለተማሪው የመማር ፍላጎት የሚፈጥሩ፣ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች አመጣጥኖ ለማቅረብ የሚያስችሉ፣ የይዘቱ አካሄድ ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከቅርብ ወደ ሩቅ የተደራጀ፣ የተማሪውን የመማር ዘዴ ወይም ስትራቴጂ የሚያሳዩ፣ መምህሩንና ተማሪውን በጋራ የሚያስተሳስሩ፣ የሚያሳትፉ ወዘተ... መሆን አለባቸው፡፡ ከላይ በመነሻው በምሁራኑ እንደተብራራው በአሁኑ ጊዜ የጽህፈት ክሂል ችሎታ በተማሪዎች ዘንድ በሚጠበቀው ደረጃ ለይ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በፊት ምሁራኑ እነደገለጹት በስፋት ይታይ የነበረው በመማሪያ መሣሪያዎች በዝግጅት ወቅት የሚከሰተው ጉድለት (ችግር) ወደ ትግበራ ሊገቡ በ2015 ዓ.ም በሙካራ ትግበራ ስራ ላይ ካሉት የትምህርት መሳሪያዎች በጥናት ሊስተካከል ይገባል፡፡

የዚህ ጥናት አጥኚ በቋንቋ መምህርነት ከሀያ አመታት በላይ ሲያገለግል ያጋጠመው ችግር ምሁራኑ ካቀረቡት የተለየ አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደዘጠነኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች አብዛኞቹ በሚያሳዝን ሁኔታ የጽህፈት ክሂል

ውድቀት ማሳያ እየሆኑ እንደሆነ መምህራን በተለይም የቋንቋ መምህራን አጥኚውን ጨምሮ ይገልጻሉ፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ስማቸውን ለመጻፍ እንኳን ሲቸገሩ፣ አንዳንድ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ማስታወቂያዎችን፣የተማሪዎች ስም ዝርዝርና ሪፖርቶችን ጽፈው ሲያቀርቡ ምን ለማለት እንደፈለጉ ለመለየት አስቸጋሪ ሆኖ ማየት የተለመደ ነው፡፡በተለይም ደግሞ የሆሄያትን ቅርጽ በተገቢው መንገድ የማይለዩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ማየት ብርቅ አይደለም፡፡

መርሀ ትምህርትን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ አመለካከት ያላቸው ቢሆንም የአብዛኞቹ ሀሳብ በይዘቱ ልዩነት አያሳይም፡፡መርሀ ትምህርት ስርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ዝግጅት ሲሆን በውስጡ ክህሎችን፣አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን፣የትምህርቱን ይዘትና አቀራረብ፣የግምገማ አማራጮችና የየክፍሉን የክፍለ ጊዜ ስርጭት የያዘ ሰነድ ነው፡፡https//advising.standford.edu የተሰኘ ድረ ገጽ መርሀ ትምህርትን "በተወሰነ የጊዜ ክልል ለሚቀርብ ትምህርት የሚውል የስራ መርሀና በትምህርቱ ወቅት ከመምህሩ የሚጠበቅ ውጤት ማሳያ ነው፡፡ ስለ ትምህርቱ ማወቅ ያለብንን አብዛኛውን የሚነግረን፣የትምህርቱ አካሄድ ምን መምሰል እንዳለበትና ከመምህሩ የሚጠበቀውን የሚጠቁም መሳሪያ ነው" በማለት አስቀምጧል፡፡ይኸው ድረ ገጽ መርሀ ትምህርት ተማሪዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ የሚጠበቀውን ውጤት ይጠቁማል፡፡ትምህርቱ የሚፈልጋቸውን ይዘቶች፣የተማሪ መገምገሚያ ዘዴዎችና ማስተማሪያ መሳሪያዎችንም ለይቶ የሚያሳይ የትምህርት መሳሪያ እንደሆነ አመልክቷል፡፡

https//shore light.com የተሰኘ ድረ ገጽ በበኩሉ መርሀ ትምህርትን ስለ አንድ ትምህርት ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች አቅርቦ የሚያሳይ ሰነድ እንደሆነ ያብራራል፡፡

Widdowson (1984:26) ሲለበስን ሲገልጹ"…በቀላል አገላለጽ መርሀ ትምህርት ትምህርታዊ ተግባራት የሚከናወኑበት፣መማርን የሚያቀላጥፍ ማስተማሪያ መሳሪያ ነው" በማለት አስረድተዋል፡፡ Wills(1990) በበኩላቸው "መርሀ ትምህርት ምን መማር እንዳለብንና እንዴት መማር እንዳለብን የሚገልጽ ሲሆን አላማው የቋንቋን ትምህርት ይዘት፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትርጉም ባለው መልኩ አዋቅሮ የሚይዝ የትምህርት መሳሪያ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡ Hachinson and Walters(1991), Dubin and Olishtain(1986), Yelden(1991) በጋራ እንደሚገልጹት መርሀ ትምህርት፣ ተማሪው ምን ይማራል፣ወይም ምን መማር ይገባዋል የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልስ ትምህርታዊ ሰነድ ነው፡፡

የተጣጣሚነት ምንነት ጉዳይ ሲነሳም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ነገሮች በመካከላቸው ሊኖር የሚችል መማሳሰል፣ መስተጋብር ወይም ተራክቦ ነው፡፡ተጣጣሚነትን በተመለከተ

CunningsWorth (1984:5) መማሪያ መጻህፍትና መርሀ ትምህርት ተያያዥና ተደጋጋፊ መሆን አለባቸው በማለት ሁለቱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ያላቸውን ቁርኝትና ተጣጣሚነት ያስረዳሉ፡፡ እኚሁ ምሁር የመማሪያ መጻህፍትይዘቶች አወቃቀርናየትምህርቱ አካሄድየሚወሰነው በመርሀ ትምህርቱ አላማ መሰረት በመሆኑ ሁለቱ ተጣጣሚ እንጂ ተቃራኒ መሆን የለባቸውም በማለት ይገልጻሉ፡፡

ተጣጣሚነትን በተመለከተ ከላይ የቀረቡት ሀሳቦች የሚነግሩን የመማሪያ መጻህፍት የሚዘጋጁት መርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበውን አላማ መነሻ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡ይህ ከተሟላ ነው መርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጻህፍቱ መካከል ተጣጥሞሽ አለ የሚባለው፡፡

ከላይ በምሁራኑ እንደተብራራው ለመጻፍ ክሂል መውደቅ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች ሊኖሩ የሚችሉ ቢሆንም እንደዚህ ጥናት አጥኚ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሃፍና ለዚሁ ክፍል የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት የጋራ የይዘት አካል የሆነው የመጻፍ ክሂል በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች የተጣጣሚነት ችግር ሊኖር ይችላል የሚል መላምት አለው፡፡ ስለዚህ ይሃው ችግር አዲስ በሚጀመሩት የትምህርት መሳሪያዎች እንዳይቀጥል በ2014 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ታትመው በያዝነው  2015 ዓ.ም ለሙካራ ትግበራ በውስን ትምህርት ቤቶች በተሰራጨ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍና መርሃ ትምህርቱ መካከል በዝግጅት ወቅት የቀረበውን የመጻፍ ክሂል የይዘት ተጣጥሞሽ ከሙሉ ትግበራ በፊት በመፈተሽ ግብኣት የማቅረብ ስራ አስፈላጊነቱ የግዴታ ነው፡፡በዚህ ጥናት ዝግጅቱ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ያመጣው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖር እንኳን የሚታይ አይደለም፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ርዕስ ለጥናት የተመረጠበት ምክንያት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው እነዚህን በ2014 ዓ ም የተዘጋጁትን የትምህርት መሳሪያዎች በሚመለከት በዚህ ርዕስ በቀጥታ ከጊዜ ጥበት የተነሳ የተጠና ጥናት ከጊዜ የሌለ በመሆኑ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ  ውስጥ የተካተቱት  የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ከክፍሉ መርሃ ትምህርት ጋር ያለቸውን ተጣጥሞሽ በመፈተሽ ክፍተቶቹን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ነው፡፡በአሁኑ ጊዜ ከመቼውም የበለጠ ተማሪዎች መጻፍን ሲያስቡ ግድየለሽ ናቸው፡፡መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት በጥንቃቄ ሲጻፉ ማየት ብርቅ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከተግባባን ምን ችግር አለው የሚል ለመጻፍ ስርዓት መበላሸት ግድ የለሽ ትውልድ እየተፈጠረ ነው፡፡መጻፍ የአፍልቆት ክሂል እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ወዘተ...እንዲገልጹና ልዩልዩ ልምምዶችን

እንዲያከናውኑ ስለሚጠበቅ፣ ክሂሉን ለማሻሻል ብዙ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ይህም ግዴታ የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎቹ በክሂሉ ውስጥ ያሉትን አላባውያን (ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ስርዓተ አጻጻፍ) በተግባር መለማመድ ስላለባቸው ነው(Nunan 1991, Ariningsih 2010):: ስለዚህ መማሪያ መጽሀፍና መርሃ ትምህርቱ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ሊታወቅ ይገባል፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት አጥኚ የ9ኛ ክፍል"አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ"በሚል ተዘጋጅቶ በሙካራ ትግበራ ላይ ባለው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ለዚሁ ክፍል ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን መጣጣም ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የመጻፍ ክሂል ይዘት ከክፍሉ መርሃ ትምህርት ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዋና አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች ተካተዋል፡፡

ሀ.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር በመመርመር ከመርሀ ትምህርቱ ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ፣

ለ.የመማሪያ መጽሀፉ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት የመጻፍ ክሂል ርዕሶች ጋር መጣጣማቸውን መገምገም፣

ሐ.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በዋናነት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አቀራረብና አደራጃጀት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር መጣጣሙን (መዛመዱን) መፈተሽ እንደሆነ ቀደም ብሎ በአላማው ላይ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

**ለመምህራን፡-**በመጽሃፉ ውስጥ የቀረቡ የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ስለሚፈትሽ መምህራን የሚሰሩበትን መማሪያ መጽሀፍ እንዲገነዘቡት ያስችላል፡፡

**ለመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች**፡-ይህ በ2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በሙከራ ትግበራ ላይ ባለው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍና መርሃ ትምህርት ላይ እየተሰራ ያለ ጥናት የመጻፍ ክሂልን አደረጃጀት ሁኔታ ስለሚፈትሽ በተለይ ለዚህ መጽሀፍ አዘጋጆች ሊኖሩ የሚችሉ ክፍተቶችን ሊጠቁም የሚችል ሲሆን በአጠቃላይ ደግሞ ለመማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች ምናልባትም የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

**ለጥናት አድራጊዎች፡-** ወደፊት በዚህና በመሰል ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት በ2014 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ ም በሙካራ ትግበራ ላይ ባለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘትና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ የተጠቃሹን ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የመጻፍ ክሂል ይዘቶችና አቀራረብ መመርመርና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችና ለክፍሉ ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር መጣጣማቸውን መገምገም ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም በጽህፈት ክሂል ዙሪያ ሊጠኑ የሚችሉ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችን አይመለከትም፡፡ ለምሳሌ የመጻፍ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለውን ቅንጅት፣ መማሪያ መጽሀፉና መርሃ ትምህርቱ ከመምህሩ መምሪያ ጋር ያላቸውን ተጣጣሚነት፣ ወዘተ…ይህ ጥናት የማይመለከታቸው ናቸው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት ወደ ሙሉ ትግበራ ባልገቡ የትምህርት መሳሪያዎች ላይ የሚደረግ ነው፡፡እነዚህን የትምህርት መሳሪያዎች በሚመለከት የተደረገ ጥናት ማግኘት የሌለ በመሆኑ ለመነሻ የሚሆን መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡እነዚህ የትምህርት መሳሪያዎች የተዘጋጁት እንደ ፌዴራል ቋንቋ እንደ መሆኑ መጠን አዘጋጆቹ በአንድ ሀገር አቀፍ የትምህርት መዕከል የሚሰሩ፣ አርታኢዎቹንም ቢሆን እንዲሁ በቀላሉ ማግኘትና መረጃ መሰብሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡የአማርኛ ትምህርት መምህራኑም ቢሆኑ የትምህርት መሳሪያዎቹን በቀላሉ የማገኘት ዕድል የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ሚኒስቴር አዲሱን ስርዓተ ትምህርት በሙካራ ደረጃ የጀመረው ከአንድ ዞን አንድ ትምህርት ቤት በመምረጥ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከሁሉም አቅጣጫ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ማግኛ መንገድ ጠባብ ነው፡፡እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ጥናቱ ቀለል ባለ መንገድ እንዳይጠና ማነቆ የሆኑ ቢሆንም የተገኘውን ሰነድ በጥልቀት በመመርመር ጥናቱ ተካሒዷል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ምንነትና አስፈላጊነት

የማስተማሪያ የመማሪያ መሳሪያዎች የቋንቋ ትምህርት የተሳካ እንዲሆን ተኪ የሌለው አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እነዚህ የትምህርት መሳሪያዎች ስርአተ ትምህርት፣ መርሀ ትምህርት፣ የተማሪው መማሪያ መጽሀፍና የመምህሩን መምሪያ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ስለመሳሪያዎቹ (በዚህ ጥናት የተካተቱት ብቻ) ምንነት፣ ባህሪያትና አይነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.1.1 የመርሀ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት

መርሀ ትምህርት ከስርአተ ትምህርት ጠበብ ያለና ከሱም የሚነሳ፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች የሚያሳይ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣ የምዘና ዘዴዎችንና መርጃ መሳሪያዎችን የሚያሳይ ሰነድ ነው (CunningsWorth 1984፣22)፡፡ እንዲሁም Dubin እና Oishtain(1996፣37) መርሀ ትምህርት ስርኣተ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር የስርኣተ ትምህርት ፍልስፍና እውን የሚሆንበት ሰነድ ነው፡፡ መርሀ ትምህርት የመማር ማስተማር ተግባር ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚተገበርበት፣ የትምህርቱ አላማዎች ግብ የሚመቱበት ሁኔታ የሚመቻችበት፣ ዝርዝር የትምህርት ዕቅድን የያዘ ሰነድ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Widdwson(1990፣129) የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለመምህራን እንደ መመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግላቸው፣ የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን በማሳየት የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዴት እንደሚተገብሩና የማስተማር ክንውኖችን እንዲያጎለብቱ የሚጠቁም መሆኑን ያበራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው መርሀ ትምህርት ማለት ከስርኣተ ትምህርት ጠበብ ያለ፣ ስርኣተ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች በግልጽ የሚያሳይ፣የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣የትምህርትን ጊዜ የሚወስን፣ የምዘና ዘዴዎችንና መርጃ መሳሪያዎችን የሚጠቁም ሰነድ መሆኑን ነው፡፡በአንድ መምህር እጅ መገኘት ከሚገባቸው ወሳኝ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል አንዱና ምናልባትም በመምህር እጅ ለምገኙ ለሌሎች የትምህርት መሳሪያዎች መሰረቱ ይኸው መርሀ ትምህርት ነው፡፡

መርሀ ትምህርት በሚቀረጽበት ጊዜ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ ዓለም (1995) እንደሚገልጹት በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

- ተማሪ አሳታፊ የሆኑ ክንውኖችን ማካተት፣
- ክንውኖቹን በተማሪ ፍላጎትና ደረጃ ላይ መመስረት፣
- ክሂሎች ተቀናጅተው መካተታቸውን ማረጋገጥና
- ክንውኖቹ በተማሪዎች ሊተገበሩ ሚችሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

መርሀ ትምህርት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ Ur (1996፣177) "መርሀ ትምህርት ለመምህራን ከሚሰጠው ጠቀሜታ ባሻገር ተያያዥነት ላላቸው ኃላፊዎች፣ ለጥናት አድረጊዎች፣ለመማሪያ መጻህፊት አዘጋጆች፣... ጠቀሜታ አለው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

Yalden (1987፣86) "መርሀ ትምህርት መምህሩ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ኃላፊነቱን በትክክል ለመወጣት እንዲችል የሚያግዝ፣ አቅጣጫን የሚመራና ለደረጃው የተዘጋጀውን ይዘት ተማሪዎች ዘንድ ለማድረስ የሚያስችል የስራ መመሪያ ነው፡፡ በመሆኑም መርሀ ትምህርት የተማሪውን ፍላጎት በክፍል ውስጥ ከሚከናወን የትምህርት ክንውን ጋር እንዲጣጣም የሚያስችል በመሆኑ ትምህርታዊ ግልጋሎትን ለህብረተሰቡ ለማበርከት ሃላፊነቱን የሚወጣበት ተደርጎ መታየት ይኖርበታል" ይላሉ፡፡

Parks and Harris (2002፣56) "መርሀ ትምህርት ለአንድ ክፍል ውስጥ የታቀዱ የትምህርት ይዘቶች በግልጽና በተሟላ ሁኔታ የሚሰፍሩበት በመሆኑ የትምህርቱ ምዕራፎችና ምዕራፎቹን ለመሸፈን የሚወስደው ጊዜ የሚወሰንበት፣ ለክፍሉ የመማሪያ መጻህፍት ይዘቶች የሚመረጡበት፣ የሚወሰኑበትና ቅደም ተከተላቸው የሚደራጅበት የማስተማሪያ መሳሪያ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

አለም (1992፣180–181)፣ Hutchinson (1987)እና Dubin and Olshtain (1986)ን በመጥቀስ የመርሀ ትምህርትን ጠቀሜታ እንደሚከተለው ዘርዝረው አስቀምጠዋል፡፡

1) ቋንቋ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ የመግባቢያ መሳሪያ በመሆኑ ይህን ረቂቅና ውስብስብ መግባቢያ መሳሪያ በቀላሉ ማስተማር ይቻላል ብሎ በደፈናው መገመት የዋህነት ነው፡፡ ይህን ረቂቅና ውስብስብ የመግባቢያ መሳሪያ ተማሪው በአግባቡ እንዲማር፣ መምህሩም በአግባቡ እንዲስተምር ለማድረግ ረቂቁና ውስብስቡ ቋንቋ በጥልቀት ተመርምሮና ደረጃ

በደረጃ ለትምህርት ሊቀርብ በሚችልበት መልኩ ተሸንሽኖ መቀመጥ አለበት፡፡ እንዲህም ሆኖ ሲቀመጥ የመማሪያ መጽሀፍ ለማዘጋጀትና ሌሎችንም የማስተማሪያ መረጃዎችን ለማሰናዳት ዕድል ይሰጣል፡፡ ለዚህም የመርሀ ትምህርት መኖር ግድ ነው፡፡

2) መርሀ ትመህርት የቋንቋ ትምህርት ዕቅድን ከመነሻው እስከ መድረሻው ጥርት አድርጎ ስለሚያሳይ የቋንቋውን ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በተመለከተ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች በራስ መተማመን ስሜታቸው ከፍ እንዲል ያግዛል፡፡

3) መርሀ ትምህርቱ የቋንቋ ትምህርት ሂደት አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት ግብ ብቻ የሚጠቁም ሳይሆን ወደ ግብ መድረሻው መንገድ ላይም ተማሪዎችና መምህራኑ እንዴት መራመድ እንዳለባቸው ጭምር የሚጠቁም ነው፡፡

4) መርሀ ትምህርት መምህራን ቋንቋን ለምን እንደሚያስተምሩና ተማሪዎች ለምን እነደሚማሩት በተዘዋዋሪ የሚገልጽ፣ ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በየትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥተው መማር እንዳለባቸው የሚያመለክት መሪ ወይም አቅጣጫ መቋሚ መሣሪያ ነው፡፡

5) መርሀ ትምህርት ማስተማሪያ መጽሀፍ ለማዘጋጀትና የማስተማሪያ መሣሪያ ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን የሚይዝ ብቻም ሳይሆን ትኩረት ሊያገኝ የሚገባውን የመልመጃ አይነትም ጭምር በመጠቆም ለቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

6) መርሀ ትምህርት በድህረ ቋንቋ ትምህርት ለሚደረገው ግምገማ መሰረትና መነሻ ሆኖ ስለሚያገለግል የቋንቋው ትምህርት ሲጠቃለል ለሚደረገው የምዘና ሂደት የመመዘኛውን መስፈርት በመጠቆም ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣል፡፧

7) መርሀ ትምህርት በአንድ ትምህርት ቤት፣ በአንድ ከተማ፣ በአንድ ክልል፣ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ያልተዥጎረጎረ፣ አንድ ወጥ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ ትምህርት ለመስጠት ዋናና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ባጠቃላይ ከማብራሪያዎቹ እንደምንረዳው የመምህርና የተማሪን ተግባራት ለይቶ የሚያሳይ፣ አጠቃላይ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ለማዘጋጀት ጠቋሚ የሆነና አንድ ወጥ የሆነ የቋንቋ ትምህርት ለማዳረስ የሚረዳ፣አንድን የትምህርት ግብ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ወደ ግብ የሚያመራውን መንገድ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ፣ የግምገማ ዘዴን በማመልከት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ቁልፍ ትምህርታዊ ሰነድ ነው፡፡

## 2.1.2. የቋንቋ መርሀ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት አላማዎች ከተነደፉና ይዘቶች ከተመረጡ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ የተመረጡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ይዋቀሩ ወይም ይደራጁ የሚለው ነው (ተስፋዬ 1981፣41)፡፡

ስለዚህ አላማን ከግብ ለማድረስ ይችላሉ ተብለው በተመረጡ ይዘቶች አማካኝነት ይመጣል ተብሎ የሚታሰበው የባህርይ ለውጥ በተግባር ይታይ ዘንድ የተመረጡ ይዘቶች በስርኣት ሊደራጁ ይገባል፡፡ ለትምህርት ይዘቶች አጥጋቢ በሆነ ስልት የመዋቀር ስኬት ሶስት ዋናዋና ጉዳዮች መሟላት እንዳለባቸው Tyler (1949፣84–85) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

### ሀ/ ተከታታይነት

ተከታታይነት የሚለው ፅሳቤ የአንድን ትምህርት ቀጣይነት ያመለክታል፡፡ ተከታታይነት በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ አንድ አይነት ዕውቀት ለማስገኘት ወይም ለማሳደግ ሲባል በተደጋጋሚ የሚመጣ የትምህርት ይዘት ነው፡፡ አንድ ትምህርት ተከታታይነት አለው ሲባል የትምህርቱ የመጨረሻ ክፍል ከቀጣዩ ትምህርት መግቢያ ጋር ግንኙነት አለው ማለት ነው፡፡

### ለ/ ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት የሚለው የይዘት አደረጃጀት ፅሳቤ ከተከታታይነት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በዚህ ፅሳቤ መሰረት የአንድ ይዘት በትምህርት ውስጥ መደጋገም ብቻ ሳይሆን የትምህርቱ ይዘት ቀድሞ ከቀረበበት ጥልቀት ወይም ክብደት በሰፋ ሁኔታ በቀጣዩ ትምህርት ላይ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ ባጠቃላይ የተማሪው የትምህርት ደረጃ እያደገ ሲሄድ የሚቀርብለት የትምህርት ይዘት ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድ ይኖርበታል ተስፋዬ (1981፡40)፡፡

### ሐ/ ቅንጅት

ቅንጅት (ውህደት) በትምህርት ይዘቶች መካከል ያለው ግንኙነትና የእርስበርስ መደጋገፍን የሚመለከት ነው፡፡ ለትምህርትነት ተመርጠው የሚቀርቡ ይዘቶች የእርስበርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው ተደርገው መደራጀት አለባቸው፡፡ ይህን ሀሳብ ተስፋዬ (1981፣41) የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች የእርስ በርስ መደጋገፉ ይዘቶቹ አንዱ ሌላውን የማዳበርና የማበልጸግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

## 2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ምንነትና አስፈላጊነት

### 2.2.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ምንነት

በጽሁፍ የሰፈረ፣ ለመማር ማስተማር የሚሆን ሀሳብና ሀሳቡን የሚያጎለብቱ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችና መልመጃዎች በጽሁፍ ከሚቀርቡባቸው የማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ዋነኛው ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ትምህርት ሚኒስቴር (1994፡14) መማሪያ መጽሀፍን "መማሪያ መጽሀፍና አብሮት የሚመጣው የመልመጃ መጽሀፍ በስርአተ ትምህርቱ ተጠቅሶ የቀረበው አብዛኛው ትምህርት የሚሽከረከርበት ማዕከላዊ ጉዳይ ነው" በማለት ይገልጻል፡፡ Ur(2006፣183) በበኩላቸው ስለ መማሪያ መጽሀፍ ምንነት ሲገልጹ "መማሪያ መጽሀፍ የምንለው በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ይዘቶችን የሚይዝ ነው፡፡ ይህም መምህሩም ሆነ ተማሪው ሊከተሉት የሚገባቸውን መርህ የሚያመለክትና ለቋንቋ ትምህርት ወሳኝ የሆነ የማስተማሪያና የመማሪያ መሣሪያ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

ተስፋዬ (1981፡86) በበኩላቸው "የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለተወሰነ ክፍል ማስተማሪያነት የሚያገለግል መሣሪያ ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ ስለ መማሪያ መጽሀፍ በምሁራኑ የቀረበው ጠቅለል ያለ ሀሳብ የሚነግረን፣የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለቋንቋ ማስተማሪያ የሚሆን ይዘት የተሸከሙ፣ ተማሪው እንዲማረው በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተጠቀመው ጉዳይ እንዲተገበር ለማድረግ ወደ ክፍል የሚያመጡ ቢያንስ የመነሻ ሃሳብ የያዙ ሰነዶች መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በየደረሱባቸው የክፍል ደረጃዎች ሁሉ በትምህርትነት የሚቀርቡ የተለያዩ ይዘቶችን በውስጣቸው ሰብስበው የያዙ፣አገልግሎታቸው ላቅ ያለና በየጊዜው ዘመኑ የሚያፈራቸውን አዳዲስ ፈጠራዎች ተከትለው እየታረሙ፣ እየተሻሻሉና እየተስፋፉ የሚሄዱ መሣሪያዎች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ጥሩ መማሪያ መጻህፍት ተመሪውን ለትምህርት የሚያነሳሱ፣ የሚቀሰቅሱና የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ጠቀሜታቸው የላቀ የትምህርት መሣሪያዎች ናቸው፡፡ Hutchison and Torres (1994) የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን አስፈላጊነት ሲገልጹ "የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለመምህሩ መምሪያ በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ ለተማሪዎች ደግሞ ደጋፊ ማስታወሻ ከመሆኑም በተጨማሪ ቋሚ የሆነ የመማር

ማስተማርን ተግባር መለኪያ መሳሪያ ነው" በማለት ያብራራሉ፡፡የቋንቋ መማሪያ መሣሪያዎችን በተላይ የመማሪያ መጻህፍትን ጠቀሜታ በሚመለከት ትምህርት ሚኒስቴር (1994፡4) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

ሀ/ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተማሪው ይማረዋል ተብሎ የተቀመጠውን ይዘት በተለያዩ

  መንገዶች እንዲማሩ ያደርጋሉ፡፡

ለ/ መምህሩ የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት በሚፈልግበት ጊዜ ማተኮር ያለበት በየትኛው ይዘት

  ላይ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

ሐ/ ቢተነተኑ በጣም ዝርዝር ሊሆኑ የሚችሉ የይዘት ዕሳቤዎችን ወይም መረጃዎችን

  ሰብስበውና አጠር አድርገው ያቀርባሉ፡፡

መ/ የመማሪያ መጻህፍት በቂ ስልጠና ያላቸውና የታላሚው ቋንቋ ችሎታ ያላቸው መምህራን

  በሌሉበት እንደ ርቀት ትምህርት ባለ ሁኔታ፣ተማሪው በራሱ መማር እንዲችል ይረዳሉ፡፡

ሠ/ ከክፍል ውጪ አመቺ በሆነ ቦታና ጊዜ የትምህርቱን ስራ ለመቀጠል ያስችላሉ፡፡

ረ/ ለብዙ ተማሪዎች ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት ደረጃ ወይም ዕውቀት ይሰጣሉ፡፡

ሰ/ መምህሩ ትምህርቱን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት አቅጣጫ ያሳያሉ፡፡

ሸ/ ስዕል፣ ካርታ፣ ሠንጠረዥ… የመሳሰሉ ነገሮችን ሊያካትት ይችላሉ፡፡

ቀ/ ማለማመጃ ጥያቄዎችን ያካትታሉ፡፡

በ/ መምህሩ የሚያስተምርበትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመፈለግና በማዘጋጀት ስራ ላይ

  የማስተማሪያ ጊዜውን እንዳያባክን ያደርጋሉ፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጻህፈት አስፈላጊነት ባጭሩ፣ በተለያዩ አካባቢዎች የሚማሩ ተማሪዎች ተመሳሳይ ዕውቀት እንዲኖራቸው የማድረግ አቅም ያላቸው ከመሆኑም በላይ ለመምህሩ የመማር ማስተማር ዕቅድ፣ ዝግጅትና ትግበራ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ጥልቅ ሀሳቦች አካተው የያዙና የተለያዩ መረጃዎችን ያቀፉ በመሆኑ የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

## 2.3. የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍ ተጣጣሚነት

ከላይ ስለመርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻህፍት ምንነት ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፣መርሃ ትምህርት በአንድ የተወሰነ የትምህርት ዓይነት ሊጠቀለሉ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችን የሚያካትት ሲሆን መማሪያ መጻህፍት ደግሞ በመርሀ ትምህርቱ የተመረጡ ይዘቶች ወደተግባር ተለውጠው ለተማሪው የሚቀርቡበት ነው፡፡

ይህን በማስመልከት Richards (1987፣2) "መርሀ ትምህርት በተግባር ሊገለጽ የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያ የሆነ የስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡ በተግባር የሚታየውም መገለጫው በሆኑ በመማሪያ መጻህፍት አማካኝነት ሲሆን ለትምህርት ውጤታማነትም ጥልቅ ድርሻ አለው" በማለት የመርሀ ትምህርትንና የመማሪያ መጻህፍትን ተጣጥሞሽ ያስረዳሉ፡፡

Dubin & Olishtain (1986፣29) እንደገለጹት መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄና ጥናት ተደርጎበት ሲሆን በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት መካተት ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች ይወስናል፡፡ ጠለቅ ሲልም ምን ማስተማር እንደሚያስፈልግ፣ እንዴት ማስተማር እንደሚቻልና በምን መልኩ መገምገም እንደሚገባ መረጃ ስለሚሰጥ የመማሪያ መጻህፍት በመርሀ ትምህርቱ መመራት እንዳለባቸው ግድ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

CunningsWorth (1984:51) መማሪያ መጻህፍትና መርሀ ትምህርት ተያያዥና ተደጋጋፊ መሆን እንዳለባቸው ከገለጹ በኋላ ቁርኝታቸውን አስመልከተው "የመማሪያ መጻህፍት ይዘቶች አወቃቀርና የትምህርቱ አካሄድ የሚወሰነው በመርሀ ትምህርቱ አላማ መሰረት በመሆኑ ሁለቱ ተቃራኒ መሆን የለባቸውም" በማለት ሀሳቡን አጠናክረዋል፡፡

ምሁራኑ እንዳተኮሩበት ሁሉ የመማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ መርሀ ትምህርቱን መከተል ግዴታ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ይህ ከሆነ ነው በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጻህፍት መካከል ተጣጥሞሽ አለ የሚባለው፡፡

## 2.4 የቋንቋ ክሂሎችና የይዘት ምንነት

የቋንቋ ትምህርት ይዘት ተማሪው እንዲማረው የተፈለገውን ዕውቀት፣ አመለካከትና ክሂሎትን የሚያመለክት ሲሆን በቋንቋ ተፈጥሮና በቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ ላይ የሚመሰረት ነው (Nunan 1988):: ከዚህ የምንረዳው የትምህርት ይዘቶች በክፍል ደረጃው በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት የተካተቱትን ርዕሰ ጉዳዮች ይመለከታል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ የትኛውን ይዘት

በየትኛው የክፍል ደረጃ እንደሚያስተምር ለማወቅ የሚያስችሉት የርዕሰ ጉዳይ ዝርዝሮች ናቸው፡፡

የቋንቋ ትምህርት አራት የክሂልና ሁለት የዕውቀት ዘርፎች አሉት፡፡ የአራቱ የክሂል ዘርፎች አብይ ትኩረት ቋንቋውን የሚማሩ ተማሪዎች ክሂሎቹን በተገቢ ሁኔታ ተለማምደው በአስፈላጊው ጊዜና ቦታ መጠቀምና መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

የአራቱን የቋንቋ ክሂሎች የይዘት ምንነት አስመልክተው Widdowson (1978፣57) ሲገልጹ "ማዳመጥና መናገር መልዕክትን ወይም ሀሳብን በቃል የመቀበያና የማስተላለፊያ ክሂሎች በመሆናቸው ቃላዊ ሲሆኑ ማንበብና መጻፍ ደግሞ በሚታዩ ምልክቶች አማካይነት መልዕክትን የመቀበያና የማስተላለፊያ ስልቶች በመሆናቸው ጽሁፋዊ ናቸው" ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ• Richards እና Rodgers (1986፣25) አገላለጽ በቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች ከሚኖሯቸው ዋናዋና አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎት ብቃት ማጎለበት ነው፡፡ይዘት የቋንቋን ትምህርት አላማ ለማሳካት በጥንቃቄ የሚመረጥ ነው፡፡ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የሚገባቸው፣እንዲያውቁ የታሰበውና እንዲያመጡ የተፈለገው የባህርይ ለውጥና ሊይዙ የሚገባቸውን ችሎታ ለማግኘት ያስችሉ ዘንድ በመርሀ ትምህርቱ ተጠቁመው በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የትምህርቱ አላባውያን ናቸው፡፡

Nunan (1988፣10) እንደገለጹት በቋንቋ ትምህርት፣ ይዘት የሚባለው ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የተፈለገው የቋንቋ ዕውቀት፣ ክሂሎት፣ አመለካከትና ዕሴቶች የሚያመለክትና መሰረቱን በቋንቋ ተፈጥሮና በቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳባዊ አመለካከት ላይ ያደረገ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ይዘት መርሀ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ፣ ተማሪዎች እንዲማሩት ታስቦና ታቅዶ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ቀርቦ እንደየክፍል ደረጃው የሚተገበር ክሂል ወይም ዕውቀት ነው፡፡

### 2.4.1.የቋንቋ ይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች

የቋንቋ ይዘት አደረጃጀት ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና ውህደት(ቅንጅት) ሊኖረው ይገባል፡፡ ከላይ በመርሀ ትምህርት ማብራሪያ በስፋት ለማብራራት እንደተሞከረው፣ ተከታታይነት አንድ የዕውቀት ዘርፍ ወይም ክሂል  በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ውስጥ ተደጋግሞ የሚመጣበትና በልምምድ ላይ የሚውልበት ሁኔታ የሚገልጽ ነው፡፡ ተለጣጣቂነት ደግሞ በቀዳሚው ይዘት ላይ መሰረት በማድረግ ስፋትና ጥልቀት በመጨመር ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዝ የዳበረ እውቀት ማስጨበጥ በሚያስችል መልኩ የተደራጀ የይዘት አደረጃጀት

መስፈርት ነው፡፡ ውህደት የሚባለው ደግሞ የቀደመው ይዘት ከቀጣዩ ጋር ተያያዥ የሚሆንበትና የቀዳሚው እውቀት ተከታዩን ለመማር መሰረት የሚሆንበት ነው፡፡ ለምሳሌ የአንቀጽን አጻጻፍ በአግባቡ የተረዳው ተማሪ ዕውቀቱን ለድርሰት ሲጠቀም፣ ድርሰት ውስጥ አንቀጽ ስላለ ዕውቀቱ የድርሰት አጻጻፍ እንግዳ እንዳይሆንበት ያደርጋል እንደ ማለት ነው፡፡

## 2.5. የመጻፍ ክሂል ምንነትና አስፈላጊነት

አማረ ተሾመ (2010) የመጻፍን ምንነት አስመልክተው የዘርፉን ምሁራን ስራዎች በመጥቀስ የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

> መጻፍ ከቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የተለያዩ ምሁራን በጽህፈት ክሂል ምንነት ዙሪያ የተለያዩ ብያኔዎችን አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህ መካከል Raimes(1983) እንደሚገልጹት መጻፍ በአንባቢ እና በጸሀፊ መካከል የሚደረግ የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ የዚህ ምሁር ብያኔ የሚያመለክተው አንድ የሚጽፍ ሰው የተሰማውን ሃሳብ፣ ስሜት ወይም ፍላጎት በጽሁፍ የሚያስፍርበት፣ እንዲሁም አንባቢው የቀረበለትን ጽሁፍ ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበትና በንባብ ሂደት ከጸሀፊው ጋር ተግባቦት ለመፍጠር የሚሞክርበት መንገድ እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል እንደ Byme(1988) አገላለጽ መጻፍ ሆሄያትን በወረቀት ላይ ከማስፈር ከፍያለና በአዕምሮ ውስጥ የሚፈልቀውን ሃሳብ በጽሁፍ መልክ ለአንባቢ አቀነባብሮ የመግለጽ ሂደትን የሚመለክት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ Nunan(1989) እንደሚያስረዱት መጻፍ፣ ሀሳብን በትዕምርት የመወከል ሂደት ነው፤ ሂደቱም መዋቅር፣ የቃላት አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህሪያቱን (ይዘት፣ የአጻጻፍ ስልት፣ የጽሁፍ ምርጫ፣ የሃሳብ አንድነት፣ ግጥምጥምነትንና ተከታታይነትን) ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የሚከናወን ውስብስብ የአዕምሮ ስራ ነው፡፡ እንደ ተስፋዬ(1981) አገላለጽ ጽህፈት የሃሳብ አቀነባበርን፣ የሃሳብ አደራደርን፣ የቃላት አመራረጥና የአገላለጽንም ስልት የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም ደብዳቤዎች፣ ድርሰት፣ የድርሰት ጭብጥ‹ ሪፖርት ወዘተ... ዋናዎቹ ጉዳዮች ሲሆኑ እነዚህን ለማጻፍ በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ደረጃ በደረጃ ለማለማመጃ የሚሆኑ መልመጃዎችን በማካተት የተማሪዎችን የመጻፍ ክህሎት ማሳደግ እንደሚቻል መረዳት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የመጻፍ ክሂል ምንነት በማስመልከት የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ የምሁራኑ ብያኔዎች አገላለጻቸው የተለያየ ይሁን እንጂ በጽንሰ ሀሳበ ደረጃ ተመሳሳይነታቸው ይጎላል፡፡ Byme(1988) እንደገለጸው መጻፍ አንባቢው ሊረዳው በሚችል መልኩ ለድምጾች ውክልና በተሰጣቸው ትዕምርቶች አማካኝነት ሀሳብን መግለጽ መቻል ነው፡፡ Nunan(1989) ደግሞ መጻፍን እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡ "መጻፍ ለተወሰነ የልምምድ ጊዜ የሚቆይና የተረጋጋ የማሰላሰልን ብቃት የሚጠይቅ ውስብስብ አዕምሯዊ ሂደት ነው፡፡"

የNunan ገለጻ እንደሚያመለክተው የመጻፍ ሂደት ውስብስብ በመሆኑ ተማሪዎች በቂ ልምምድ አድርገው የጽህፈትን ክሂል እንዲያዳብሩ የሚዘጋጁት ይዘቶች ምቹና ሳቢ መሆን አለባቸው።

Flower and Hayes (1977) እንደሚሉት መጻፍ በአንድ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን ለመተግበር በቂ የመለማመጃ ጊዜ የሚፈልግ ነው። በመለማመጃ ሂደቱም ጸሃፊው በጽሁፉ ማስተላለፍ የፈለገውን ሀሳብ በሚገባና በትክክለኛው ሰዋሰዋዊ መዋቅር መጠቀምን ያጎለብትለታል። ይህን ለማሳካት በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የሚካተቱ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ተመጣጣኝ ሆነው መቅረብ ያስፈልጋል።

Sperling and Freedman (2001) "ተማሪዎች በጽህፈት ልምምድ እየገፉ ሲሄዱ ደረጃቸውን በሚመጥን ሁኔታ መጽሀፍ እንዲያነቡና ስላነበቡት ርዕስ ጉዳይ እንዲጽፉ በሚያደርጉ፣ አንድን ጽሁፍ ካነበቡ በኋላ ያነበቡትን በየራሳቸው አባባል እንዲጽፉ በሚያደርጉ፣ አንድን ስዕል በማሳየት ከስዕሉ የተገነዘቡትን እንዲጽፉ የሚያደርጉ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል" ሲሉ አበክረው ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ አስመልክተው Mercer and Mercer(1989)፣ Hami(1986)ን በመጠቀስ እንደሚገልጹት መጻፍ በዋነኛነት ሶስት ጠቀሜታዎችን ያስገኛል። የመጀመሪያው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለመጻፍ ትምህርት ግንዛቤ አግኝተው ልዩ ልዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያስችላል፤ያገኙትም ግንዛቤ መጻፍን ለሚጠይቁ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ሁለተኛው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያገኙትን ዕውቀት መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጪ ሊያከናውኗቸው የሚችሏቸውን ተግባራት (ማመልከቻ መጻፍ፣ ቅጾችን መሙላት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ወዘተ...) ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲወጡ ያስችላል። በሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎች የፈጠራ ጽሁፎችን ማለትም፣ ግጥሞች፣ ልቦለዶች፣ ረጃጅምና አጫጭር ታሪኮች ወዘተ... መጻፍ እንዲችሉ አስተዋጽኦ ያደርግላቸዋል።

ባጠቃላይ ከቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የመጻፍ ትምህርት የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን፣ የአጻጻፍ ስልትን፣ የሀሳብ አደረጃጀትን፣ የሰዋሰው ስርአትን ወዘተ... የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ፣ ተማሪዎቹ እነዚህን ተግባራት በማከናወን የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችል መሆኑን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርታዊ ክንውኖች ውስጥ የተገኙ የመጻፍ ዕውቀቶችና ልምዶችን ትምህርታዊ ባልሆኑ አውዶች ውስጥ ተጠቅሞ ልዩ ልዩ ተግባራትን

ለማከናወን አቅም ይሆናሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ያገኙትን ዕውቀት ከክፍል ውጪ ባለው አውድ እንዲጠቀሙ ለማስቻል የመጻፍ ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል፡፡

### 2.5.1.የመጻፍ ክሂል ትምህርት

ጽህፈት ሲታሰብ ከአንባቢ ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊነቱን አስመልክተው Raimes (1983፣3) ጽህፈት፣ ሰዎች በጊዜና በቦታ ሳይገደቡ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካኝነት ከማግባባቱም በላይ ለትምህርት መማሪያ፣ ለሀሳብ መለዋወጫና ለመሳሰሉት ነገሮች እንደሚያገለግል ይገልጻሉ፡፡ ይህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቱ ደግሞ በትምህርትነት እንዲሰጥና እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል፡፡ እንዲሁም Celce Murcia(1991፣241) በበኩላቸው ተማሪው በተሸለ ሁኔታ በቋንቋው እንዲጠቀምና የተግባቦቱን ሂደትም በጥልቀት እንዲመረምር ያደርገዋል ይላሉ፡፡ ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረደው ተማሪው ቋንቋውን በጥሩ ሁኔታ እነዲጠቀም ያስችለዋል ሲባል በጽህፈት ክሂል አማካኝነት ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ማስቻሉ ነው፡፡ Ur(1996፣168) የጽህፈትን ትምህርት ከግለሰባዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንጻር ይመለከቱታል፡፡ ግለሰባዊ ፋይዳው አመለካከትን ከመግለጽ፣ የተጻፉ ሰነዶችን ከመመርመርና አዕምሯዊ ተግባራትን ከመፈተሽ አንጻር ሲመለከቱት ማህበራዊ ፊይዳውን ደግሞ የማህበረሰቡ የሆኑ የተለያዩ ታሪካዊ፣ ባህላዊ መገለጫዎችን፣ ስነ ጽሁፋዊ ስራዎችንና የመሳሰሉትን ለመሰነድ ካለው ፋይዳ አንጻር ቃኝተውታል፡፡ በመሆኑም ጽሁፍ ለግለሰብም ሆነ ለህብረተሰቡ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች አንጻር ያለው ፋይዳ ጉልህ መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 2.5.2.የመጻፍ ክሂል ትምህርት አላማ

መጻፍ በትምህርትነት የሚሰጠው ለተለያዩ አላማዎች እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከነዚህም ምሁራን ውስጥ የተወሰኑትን በመጥቀስ በአላማነት ያስቀመጧቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር እንመልከት፡፡

እንደ Raimes(1983) ገለጻ ተማሪዎች መጻፍን የሚማሩባቸው አላማዎች አረፍተነገርን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት፣ ዕውቀትን ለማግኘት እንዲሁም በዕለትተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየት ሲባል የመጻፍ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ምሁሩ የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ርቱዕነትንና ትክክለኛነትን ይጠቅሳሉ፡፡ ርቱዕነት በሂደት ሊዳብር የሚችል የመጻፍ ትምህርት አንዱ አቅጣጫ ሲሆን፣ ተክክለኛነት ደግሞ በታላሚው ቋንቋ መዋቅር (ሰዋሰው) ላይ ትኩረት ያደረገ የትምህርት

ሌላኛው አቅጣጫ ነው፡፡ በመሆኑም በመጻፍ ትምህርት ሂደት በቋንቋው ሰዋሰዋዊ ይዘት ላይ ትኩረት የሚደረግ ከሆነ ትክክለኛነትን ሲጠቁም፣የመጻፍ ትምህርትን በልዩልዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ተማሪዎቹ እንዲማሩ የማድረግ ተግባር ደግሞ ርቱዕነትን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Heaton (1991) የመጻፍ ክሂልን የመማር አላማ ከንዑሳን ክሂል አላማዎች ጋር በማያያዝ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፣ የመጻፍ ክሂልን መማር የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን (ተገቢነት ያላቸውን አረፍተነገሮች መጻፍ፣ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ ላይ የመጠቀም፣ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ የመምረጥ፣ የማመንጨት እና አሰፋፍቶ የመግለጽ፣ ተፈላጊ የሆነውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የአረፍተነገርና የአንቀጽ አወቃቀር ስርአትን ጠብቆ የመጻፍ እንዲሁም መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም የመለየት ተግባርን ይጠይቃል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ምሁራን ዕይታዎች መረዳት እንደሚቻለው መጻፍ ከአንባቢ ጋር ተግባቦት ለመፍጠር፣ አዳዲስ ዕውቀቶችን ለማግኘት፣ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በውስጡ ያለውን አመለካከት ለመግለጽና ለመደገፍ ልዩልዩ አዕምሯዊ ተግባራትን ለመወጣት እንዲሁም በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ሰዋሰዋዊ እና ተግባቦታዊ ክንውኖች ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚካሄድ ጥረት እንደሆነ ነው፡፡

ባጠቃላይ መጻፍ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡፡

**ሀ. የንግግር ችሎታን ያዳብራል፡፡**

ንግግር በሚደረግበት ወቅት ዋናዋና ነጥቦችን በጽሁፍ በመያዝ ተናጋሪው እንዳይረሳ ለማድረግ አጋዥ ይሆንለታል፡፡ በተጨማሪም የንግግር ፍሰት የተጠበቀ ወይም ወጥ እንዲሆንና እንዳይቆራረጥ ነገሮችን በስርዓት አስቀድሞ አደራጅቶ ለመያዝ ያስችላል፡፡

**ለ. መጻፍ መማርን ያበረታታል፡፡**

የትምህርት ባለሙያዎች እንደሚሉት ጽህፈት በራሱ ዕውቀት ነው፡፡ ሰው በጽህፈት ትምህርት አማካኝነት ይማራል፡፡ በጽሁፍ ስለሚገልጸው ነገር ያስባል፤ ሌሎችን ይጠይቃል፤ መልስ ለማግኘት ይሞክራሉ፡፡ የራሱንም አሳክቶ ለማቅረብ ይጥራል፤ በዚህ ሂደት አስቀድሞ ከነበረው የበለጠ ዕውቀቱ የጨመረና የሰፋ ይሆናል፡፡

**ሐ. ስነልቦናዊ እርካታ ይሰጣል፡፡**

በማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ከሚታዩ እውነታዎች መካከል ፊርማን በአብነት ብንወስድ ሁኔታውን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ ቀለም በጣታቸው ነክረው የሚፈርሙ ሰዎች፣ጽፈው

መፈረም ላለመቻላቸው የሚሰጡት ምክንያት የበታችነትን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን ባንጻሩ ስማቸውን ጽፈው መፈረም የሚችሉ ሰዎች "ዕድሜ ለ…እስከነአባቴ ጽፌ መፈረም ችያለሁ" ብለው በመናገር ሲደሰቱ አፅምሯዊ እርካታቸውን በህሊናችን ማየት እንችላለን፡፡

**መ. የመጻፍ ትምህርት ሌሎች ክሂሎችንም ያዳብራል፡፡**

ከላይ እንደተጠቀሰው ጽህፈት የንግግር ችሎታን ለማዳበር ይረዳል፡፡ ተናጋሪው ስለሚያቀርባቸው ዝርዝር ጉዳዮች አስቀድሞ ነጥቦቹን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ እንዲያደራጅ የሚረዳው አጋዥ ሀይል ጽህፈት ነው፡፡ ከዚህም የንግግርና የጽህፈት ተደጋጋፊነት ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል ንግግር ሲደረግ ሀሳብ ሳይቆራረጥ ወይም ሳይዘበራረቅ ወጥነቱን እንደጠበቀ እንዲሄድ ለማስቻል አሁንም የጽህፈት አስተዋጽኦ ወሳኝነት አለው፡፡ ይህን ዕውነታ የበለጠ የሚገልጽ በሀገራችን አንድ አባባል አለ፡፡ "በቃል ያለ ይረሳል፣ በጽሁፍ ያለ ይወረሳል" የሚል፡፡ ከዚህ አባባል የንግግርን ህልውና ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ለማቆየት ከሚያስችሉት መንገዶች ለምሳሌ ከፊልምም ሆነ ከቪድዮ ቀደምትነት ያለው ጽህፈት መሆኑን እንረዳለን፡፡

ጉዳዩን ጠቅለል አድርገን ካየነው በመናገር፣ በማዳመጥና በማንበብ የምናገኛቸው የተለያዩ እውቀቶች ጠንካራ መሰረት ሊይዙ የሚችሉት በጽህፈት ክሂል አማካይነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

**ሠ. የመጻፍ ትምህርት ለምርምር ስራ አጋዥ ኃይል ነው፡፡**

ማንኛውንም የምርምር ስራ ለማከናወን የጽህፈትን የንባብ ክሂሎችን በተቻለ መጠን አቅም በፈቀደ ሁሉ ማዳበር ወሳኝነት ያለው ነገር ነው፡፡ ይህም ሲባል በምርምር ሂደት የተደረሰባቸውን የተለያዩ ግኝቶች ማወቅና መረዳት የምንችለው በማንበብ ሲሆን የራሳችንን ፈጠራና ግኝት የሆኑትን ደግሞ ለሌሎች የምናስተላልፈው በጽህፈት አማካይነት ነው፡፡

በተለይ ትምህርታዊ ለሆኑ ልዩ ልዩ ምርምሮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማጠናቀርና ለዋቤነት እንዲያገለግል መዝግቦ መያዝ የሚቻለው በጽህፈት አማካይነት ነው፡፡ በተመሳሳይ የአንድ ምርምር ወይም ፈጠራ ባለቤት የሆነ ሰው (ተመራማሪ፣ ሰይንቲስት) የስራ ውጤት ከሀገር ሀገር ወይም ከቦታ ቦታ የሚዘዋወረውና የባለቤትነት መለያም ሊያገኝ የቻለው በጽህፈት አማካኝነት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

በአጠቃላይ መጻፍ ራስን ከመግለጽ፣ ስለ ሌሎችም በጥልቀት ከመረዳትና ከመዘገብ አንጻር ትልቅ ፊይዳ አለው፡፡ በተላይም መረጃን ከግለሰብ ወደ ግለሰብ፣ ወደ ቡድን ወይም ወደ

ህብረተሰብ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ፣ ይዞ በማኖርና በማቆየት አስተማማኝነቱ ድንቅ የሚያስብል ነው፡፡

### 2.5.3 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ግብ መቺ መሆን የሚችሉት አንዱ ሌላውን እያጠናከረ በስርአት ሲደራጁ ነው፡፡ በስርአት የተደራጀ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ልምድ ቀዳሚው ለተከታዩ መሰረት በሚሆን መልኩ ሊዋቀር ስለሚችል ውጤታማ ትምህርት ለማግኘት ከማገዙ በተጨማሪ ተማሪው ቀድሞ ያልተገነዘበውን እንዲገነዘብ፣ በመጀመሪያ ያገኘው ትምህርት ተከትሎ የሚመጣውን ትምህርት ስለሚያዳብረው እንዲያግዘው ነው፡፡ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሲደራጁ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደገ ሊዋቀሩ ይገባል፡፡

## 2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠው ርዕስ ጥናት ከመጀመሩ በፊት ከርዕሱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደሙ ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዷል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በ2014 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ፣ በ2015 ዓ.ም  በጥቂት የሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተሞከረ ባለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የጽህፈት ክሂል፣ ለክፍሉ በተመሳሳይ ጊዜ ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት የጽህፈት ክሂል ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ላይ ያተኮረ በመሆኑ በተመሳሳይ ርዕስ የተሰራ ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ሆኖም የይዘት ተቀራራቢነት ካላቸው ቀደምት ስራዎች መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ካላቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት አንጻር እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ጽጌ(1992) "ለጽህፈት ክሂል የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል?" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቀረበ ጥናት የሚዳስሰው ከ5ኛ--8ኛ ክፍል በአድስ አበባ ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁት የአማርኛ መጻህፍት ላይ የይዘት ትንተናና ግምገማ አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው የደረሱበት ማጠቃለያ፣ በአራቱም ክፍሎች የጽህፈት ክሂሎችን አስመልክቶ የቀረበው የተለጣጣቂነት መስፈርት በአግባቡ ስራ ላይ ኣለመዋሉንና ለችግሩም አብይ ምክንያት የሆነው ይዘቶቹ የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥኑ ሆነው አለመመረጣቸው ነው፡፡ የጽጌን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሚያደርገው የጽህፈትን ክሂል መመልከታቸው ሲሆን የሰፋው ልዩነታቸው ደግሞ ይህኛው ጥናት የተማሪውን መጽሃፍ የጽህፈት ክሂል በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረበው የጽህፈት ክሂል ጋር አገናዝቦ ተጣጥሞሹን በመፈተሽ ነው፡፡

ሌላው አስቴር (2007) "በ2001 ዓ.ም በተዘጋጀው የ11ኛና 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ጋር ያላቸውን የይዘት ዝምድና መፈተሽ" በሚል ርዕስ በሰሩት ጥናት ላይ ሊታሰቡ ይገባል ያሏቸው ነጥቦች፡- በዚህ ጥናት ላይ ለታየው ችግር መነሻው የመጻህፍቱ አዘጋጆች በይዘት መረጣው ላይ አለመሳተፍ፣ የይዘት አደረጃጀቱ አልፎ አልፎ ከቀላል ወደ ከባድ አካሄድ አለመከተል፣ጥቂት ይዘቶች ደግሞ የቋንቋ ትምህርት አደረጃጀት መርህን አለመከተል… ጥቂቶቹ ናቸው። ሆኖም የአስቴርን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሚያደርገው ነጥብ መርሃ ትምህርትን ለመፈተሽ መሞከሩ ሲሆን የሰፋው ልዩነቱ ደግሞ ይህኛው ጥናት የመርሃ ትምህርቱን የጽህፈት ክሂል ይዘት ከመማሪያ መጽሀፉ የጽህፈት ክሂል ብቻጋር መጣጣም ያለመጣጣሙን በመፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።የአስቴር ጥናት ግን በይዘቱ ከዚህኛው የሰፋ ነው። ምክንያቱም ያተኮረው በ11ኛና በ12ኛ ክፍሎች አጠቃላይ ይዘቶች ነው።

ንጉሱ(1998) "በ1990 ዓ.ም የታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለክፍል ደረጃው በ1991 ዓ.ም ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። አላማውም በ1990 ዓ.ም የታተመው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መርሃ ትምህርት አላማና ይዘት ትንተና በ1991 ዓ.ም ከተዘጋጀው የክፍሉ መማሪያ መጽሀፍ ጋር ያለውን መጣጣም መፈተሽ ነው። የንጉሱ ጥናት ከዚህ ጋር ያለው ተመሳሳይነት መርሃ ትምህርቱን መፈተሹ ሲሆን የፈተሸበትን ጥልቀት ያህል ይህኛው ጥናት አልሄደም። ምክንያቱም ይህኛው ጥናት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያስተያየው ከይዘቶች መካከል የጽህፈት ክሂልን ብቻ መርጦ ሲሆን የንጉሱ ጥናት ግን ሁሉንም ይዘቶች የሚያስተያይ በመሆኑ ልዩነቱ በጣም የሰፋ ነው።

ደረሰ (2012) "በ9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፈት ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ፍተሻ" በሚል የቀረበው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር መመሳሰል ያለው ይመስላል። የሁለቱም የአጠናን ሂደት የሰነድ ፍተሻ ዘዴን ይከተላል። ሆኖም ልዩነታቸው፡- የደረሰ ጥናት የጽህፈት ክሂል ብቻውን በመጻህፍቱ ውስጥ እንዴት እንደተደራጀ የሚፈትሽ ሲሆን ይህኛው ጥናት የደረሰን ጥናት እንዳለ በመምሰል በ2014 ዓ.ም.የተዘጋጀውን የ9ኛ ክፍል አማርኛ መጽሀፍ የጽህፈት ክሂል በተመሳሳይ ጊዜ ለዚሁ ክፍል ከተዘጋጀው መርሃትምህርት የጽህፈት ክሂል ጋር መጣጣሙን መፈተሽ ላይ ያተኮረ ስለሆነ ልዩነታቸው የሰፋ ነው።

ባጠቃላይ ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት የጥናት ውጤቶች ጋር የሚጋራው ጉዳይ፣ እነዚህ ጥናቶች የመጻፍን ክሂል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የነኩና የተነተኑበትን ሂደት ሲሆን ሰፊው ልዩነት ደግሞ ይህ ጥናት ምንም ባልታዩና ባልተጠኑ የ2014 ዓ.ም ህትመት ውጤት በሆኑ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሃ ትምህርትና የተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ

ያለውን የጽህፈት ክሂል መጣጣም የተማሪው መጽሀፍና መርሀ ትምህርቱ ለሙሉ ትግበራ ለሁሉም የዘጠነኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች ከመሰራጨታቸው ቀድሞ መፈተሽ እንደመሆኑ መጠን በመምህር መምሪያ ውስጥ የተካተተው የትምህርት መሳሪያ መርሀ ትምህርት መባል ሲገባው ስርዓተ ትምህርት ተብሎ መቀመጡ፣የጽህፈት ትምህርት ርዕስና መልመጃዎች በመርሀትምህርትና በተማሪው መጽሀፍ በአንዱ በክፍል አራት በሌላው በክፍል አምስት በመደልደል ያመጡት የተጣጣሚነት ችግር፣ መርሀ ትምህርቱ "ድርሰት መጻፍ"ብሎ ርዕስ ሲያቀርብ በተማሪው መጽሀፍ "አንቀጽ ጻፉ" የሚሉ መልመጃዎች መገኘታቸው፣አዲሱ ስርዓተ ትምህርተ ትምህርት ለይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ መሆኑ መረጋገጡ፣በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የተነፈገው በሚመስል ደረጃ እየተዳከመ ያለውን የጽህፈት ትምህርት ለማጎልበት ለ9ኛ ከተዘጋጀው አጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት ለአንቀጽና ድርሰት 62.5 በመቶውን ድርሻ መስጠቱ…የዚህ ጥናት ግኝት መሆኑ ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ጋር ያለውን ልዩነት  የሰፋ ያደርጋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ትኩረት በ2014 ዓ.ም አዲስ በታተሙት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና በዚሁ ጊዜ ለክፍሉ በተዘጋጀው መርሃትምህርት ውስጥ የሚገኘውን የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ ንድፍ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ ናሙና አመራረጥ፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና መረጃ መተንተኛ መንገዶች ተካተዋል፡፡

## 3.1. የጥናቱ ንደፍ

ይህ ጥናት በመማሪያ መጽሀፍና በመርሃ ትምህርት ውስጥ ያለውን የጽህፈት ክሂል ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ መጣጣም አለመጣጣሙን መፈተሻ ነው፡፡ ጥናቱ መረጃዎችን በገለጻና በማብራሪያ ስልት የሚያቀርብ ስለሆነ ገላጭ የምርምር ንድፍን ይከተላል፡፡ ገላጭ ንድፍን በተመለከተ ጥቂት የማይባሉ ምሁራን ብያኔያቸውን አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ያለው (2009) ገላጭ ምርምርን ሲገልጹ፣"ገላጭ የምርምር ንድፍ ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ነባራዊውን ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚቀርብበት ንድፍ ነው" ብለዋል፡፡በዚህ መሰረት የጥናቱ ንድፍ የገላጭ ምርምር ንድፍ ነው፡፡

## 3.2.የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2014 ዓ.ም ለ9ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለክፍሉ ከተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ የመጻፍ ክሂል ጋር ያለውን ተጣጣሚነት መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ወሳኝ የመራጃ ምንጮች የ2014 ዓ.ም ዕትም የሆኑት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ፣ለዚሁ ክፍል በዚሁ ዘመን የተዘጋጀው የአማርኛ መርሃ ትምህርትና መምህራን ናቸው፡፡

## 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የተተኮረበትን የሁለቱን የትምህርት ሰነዶች የጽህፈት ክሂል የይዘት መጣጣም ለመፈተሽ ተመራጩ መሣሪያ ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻ በተጨማሪ መረጃውን ይበልጥ ተዓማኒ ለማድረግ በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ከመምህራን መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.3.1. የሰነድ ምርመራ

ለዚህ ጥናት በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ የሆነው የሰነድ ምርመራ ሲሆን ሰነዱም የተገኘው ለጥናቱ ከተመረጡት የ2014 ዓ ም ዕትም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍና በዚሁ ዘመን ለክፍሉ ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ነው፡፡ የሰነድ ምርመራው የተከናወነው በየምዕራፉ ያሉትን የመርሀ ትምህርትና የተማሪው መጽሀፍ የጽህፈት ይዘቶች ለይቶ በሰንጠረዥ በማደራጀትና ተጣጣሚነታቸውን በማሳየት ነው፡፡

### 3.3.2. ቃለ መጠይቅ

አጥኚው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመው ሌላው መሣሪያ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቁ በቀጥታ የሚሳተፉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡በከምባታ ጠምባሮ ዞን አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በሙካራ ደረጃ ከሚሰጥበት ትምህርት ቤት በ9ኛና በ10ኛ ክፍሎች አማርኛ ከሚያስተምሩ ስድስት መምህራን መካከል ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ የሆኑት አራቱ ተለይተዋል፡፡የቀሩት ሁለት መምህራን ፈቃደኛ ያልሆኑበት ምክንያት አንዱ መምህር ለጥናቱ የቀረቡት የትምህርት መሳሪያዎች አዲስ በተዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት መሰረት የቀረቡና ለሙካራ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ላሉ የቋንቋ መምህራን በ"ሶፍት ኮፒ" እንዲጠቀሙ ሆኖ በመጽሀፍነት ተዘጋጅቶ ያልተሰራጨ ስለሆነ ጫናውን ላለመሸከም ስለወሰነ ሲሆን ሁለተኛው መምህር ማየት የተሳነው በመሆኑ ነው፡፡ የቃለ መጠይቁም አላማ የመርሀ ትምህርቱ የጽህፈት ክሂል ይዘት ከመማሪያ መጽሀፉ የጽህፈት ክሂል ይዘት ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን ለመፈተሽ ነው፡፡

### 3.3.3. የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በሙካራ ትግበራ ላይ ባሉት መጻህፍት ወደ ሙሉ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የተካሄደ እንደመሆኑ መጠን በናሙና ውስጥ የገቡት መምህራንና ትምህርት ቤቶች ብዛት ውስን ነው፡፡ የንሞና ዘዴውም ጠቅላይ ንሞና ዘዴ የሚባለው ነው፡፡ ያለው (2009) "ተመራማሪው ያገኛቸውን ሁሉንም የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድረጎ ሲወስድ ጠቅላይ ንሞና ይባላል" በማለት እንዳብራሩት፣የዚህ ጥናት አቅራቢ በመምህርነት እያገለገለ ያለው በከምባታ ጠምባሮ ዞን ውስጥ ነው፡፡ በዞኑ ውስጥ የአዲሶቹ የ2ኛ ደረጃ መጻህፍት የሙካራ ትግበራ እየተደረገ ያለው በዱራሜ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ህዳሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የተመረጠው ትምህርት ቤት ዱራሜ ህዳሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ለቃለ መጠይቁ የተመረጡትና መረጃ የሰጡት የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን ናቸው፡፡ምክንያቱም በትምህርት ቤት ደረጃ የትምህርት መሳሪያዎቹን በውስን መጠንም ቢሆን እንዲያገኙ መንግስት ያቀረበው ለመምህራን ነው፡፡ቤተ መጻህፍት ውስጥ የሚቀመጥ ቅጂ የለውም፡፡በዚህ መሰረት ለቃለ መጠይቁ የተመረጡትም መምህራን የዚሁ ትምህርት ቤት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡የመምህራኑ መረጃ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡-ለቃለ መጠይቅ የተለዩ መምህራን መረጃ

| ተ.ቁ | የመምህሩ/ርቷ መለያ | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | የሚያ/የምተስተምርበት ክፍል | ጠቅላላ አገልግሎት | የአማርኛ ትምህርት አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀ | ወ | BA | 9ኛ | 30 | 30 |
| 2 | ለ | ሴ | MA | 9ኛ | 22 | 9 |
| 3 | ሐ | ወ | MA | 10ኛ | 21 | 12 |
| 4 | መ | ሴ | BA | 10ኛ | 33 | 33 |

## 3.4.መረጃ የመተንተን ዘዴ

ያለው (2009) ከመዛግብት፣ከምልከታና ከቃለ መጠይቅ የሚሰበሰቡ መረጃዎች አይነታዊውን የመረጃ አተናተን ዘዴ መጠቀም እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ ስለሆነ መረጃው የተነተነው በአይነታዊው የአተናተን ዘዴ ነው፡፡የትንተናው አካሄድ በመጀመሪያ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በተለይ በሰንጠረዥ ተለቅመው ከወጡ በኋላ የመማሪያ መጽሀፉም የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በተመሳሳይ መልኩ በሰንጠረዥ ተለቅመው በመውጣት ከርዕሰ ጉዳይ ከይዘትና መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ መርህ አንጻር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1. የሰነድ ፍተሻ መረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በ2014 ዓ ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ ም በሙካራ ስርጭት ላይ በሚገኘው የዘጠነኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ውስጥ ለመጻፍ ክሂል የቀረበውን ይዘት ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ካለው የጽህፈት ክሂል ትምህርት ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ በመተንተን አጥኚው እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

#### 4.1.1. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መርሀ ትምህርት አጭር መግለጫ

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት በ2014 ዓ ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን ለክፍሉ በተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ ከምዕራፍ አስር ቀጥሎ በመጨረሻዎቹ ገጾች አካባቢ ይገኛል፡፡ በውስጡም ለአመቱ ትምህርትነት የቀረቡ አስር ምዕራፎች ተጠቁመዋል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍም የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ የምዕራፉ አላማዎች፣ የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕሰ ጉዳዮች (ይዘት)፣ የመማር ማስተማር ስነ ዘዴ ጥቆማ፣መርጃ መሳሪያና ግምገማን አካቶ ይዟል፡፡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት 88 አጠቃለይ አላማዎች፣ 97 ዝርዝር አላማዎችና 85 ዝርዝር ይዘቶች አሉት፡፡88ቱ አጠቃላይ አላማዎች በመርሀ ትምህርቱ መቅረባቸው በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ መግቢያ በመጀመሪያ አንቀጽ የመጨረሻ አረፍተ ነገር ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ በየምዕራፉ መጀመሪያ ላይም ለንባብና ለማዳመጥ የሚሆኑ ሁለት ሁለት የምንባብ ርዕሶች ተጠቁመዋል፡፡

#### 4.1.2.በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት አጠቃላይ ይዘቶች ትንተና

ለዚህ ጥናት አጥኚው ያተኮረው የ2014 ዓ ም የዘጠነኛ ክፍል ዝግጅት በሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና በተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ባለው የመጻፍ ክሂል ይዘትና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ተጣጥሞሽ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያነት የቀረቡትን አጠቃላይ ይዘቶች አንዱን ከሌላው ጋር በማነጻጸር በሚከተለው ሰንጠረዥ አቅርቧል፡

ሠንጠረዥ፡-2 ለ9ኛ ክፍል አዲስ የተዘጋጀው የአማርኛ መርሀ ትምህርት አጠቃላይ ርዕሰጉዳዮች

| ምዕራፍ | ክፍል 1 | ክፍል 2 | ክፍል 3 | ክፍል 4 | ክፍል 5 | ክፍል 6 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አንድ | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ሁለት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ሶስት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| አራት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| አምስት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ስድስት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ሰባት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ስምንት | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |
| ዘጠኝ | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ስነጽሁፍ |
| አስር | ማዳመጥ | ንግግር | ንባብ | ጽህፈት | ቃላት | ሰዋሰው |

ከላይ በሠንጠረዥ 2. የቀረበው ዝርዝር የሚያመለክተው የዘጠነኛ ክፍል መርሃ ትምህርት በአስር ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ ስድስት ስድስት ክፍሎች አሉት፡፡በድምሩ የመርሃትምህርቱ ይዘቶች ብዛት ስድሳ ነው፡፡ከአስር ምዕራፎች የዘጠኙ ይዘቶች በአይነትም ሆነ በቅደምተከተል ተመሳሳይ ሲሆኑ፣አቀማመጣቸውም ክፍል አንድ ማዳመጥ፣ ክፍል ሁለት ንግግር፣ ክፍል ሶስት ንባብ፣ ክፍል አራት ጽህፈት፣ ክፍል አምስት ቃላትና ክፍል ስድስት ሰዋሰው ናቸው፡፡ ልዩነት ያሳየው ምዕራፍ ዘጠኝ ብቻ ሰዋሰው የሚለው ክፍል የለውም፡፡ በምዕራፍ ዘጠኝ፣ ክፍል ስድስት፣ በሰዋሰው ይዘት ምትክ ስነጽሁፍ የሚል ይዘት ተጽፎ ይገኛል፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉት ይዘቶች በሙሉ ተመሳሳይ የይዘት ስርጭት በተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንዲሰፍሩ ተደርጎ ይገኛል፡፡

የዚህ ጥናት አጥኚ ያተኮረው በመጻፍ ክሂል ላይ ስለሆነ የመጻፍ ክሂልን ስርጭት በተላይ ተንትኖ አቅርቧል፡፡ የጽህፈት ክሂል እንደ ሌሎች ክሂሎች ሁሉ በአስሩም ምዕራፎች ተሰራጭቶ ይገኛል፡፡ የጥናቱ ትኩረት ክሂሎችን ማነጻጸር ሳይሆን አንዱ የመጻፍ ክሂል አዲስ በ2014 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር በመታተም በያዝነው አመት ለሙከራ በሀገራችን በጥቂት ትምህርት ቤቶች እየተሰራባቸው ባሉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና

ለተመሳሳይ ክፍል በተመሳሳይ ጊዜ በተዘጋጀው መርሃትምህርት መካከል ያለውን የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ ሆኖም ክሂሉ ከሌሎች አንጻር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የያዘው ሽፋን እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡-አዲሱ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሃትምህርት አጠቃላይ ርዕሶች ስርጭት

| ተራ ቁጥር | የይዘቱ አይነት | ይዘቱ የቀረበበት ምዕራፍ ብዛት | የይዘቱድግግሞሽ በ% |
|---|---|---|---|
| 1 | ማዳመጥ | 10 | 16.66 |
| 2 | መናገር | 10 | 16.66 |
| 3 | ንባብ | 10 | 16.66 |
| 4 | ጽህፈት | 10 | 16.66 |
| 5 | ቃላት | 10 | 16.66 |
| 6 | ሰዋሰው | 9 | 15 |

ከላይ የቀረበው የመርሃ ትምህርት አጠቃላይ የይዘት ስርጭት የሚያሳይ ሠንጠረዥ የሚጠቁመው፣ የጽህፈት ክሂል 1.6% የስርጭት ሽፋን ካለው በ9ኛው ምዕራፍ ብቻ ስነጽሁፍ በሚል ከቀረበው ይዘት ውጪ ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተመጣጣኝ (16.66%) የስርጭት ሽፋን እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 4.1.3. የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙ የመጻፍ ክሂል ርዕሰ ጉዳዮች ስርጭት

የሚከተለው ሠንጠረዥ የዘጠነኛ ክፍል መርሃትምህርት የተካተቱ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ርዕሰ ጉዳዮች ያሣያል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- የ9ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ በየምዕራፉ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ርዕሰ ጉዳዮች

| ምዕራፍ | በየምዕራፉ ያለው የጽህፈት ክሂል ዝርዝር ርዕሶች | የተሰጣው ትኩረት በክፍለ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | አንቀጽ መጻፍ፣በባዶ ቦታ ቃላትን በመጻፍ አረፍተነገሮችን ሙሉ ማድረግ | 1.5 |
| 2 | ገላጭ ድርሰት መጻፍ፣ምሳሌያዊ አባባሎችን በጽሁፍ ማብራራት | 1 |
| 3 | ድርሰት መጻፍ | 1 |
| 4 | ዘገባ መጻፍ | 1 |
| 5 | ገላጭ ድርሰት መጻፍ | 1 |
| 6 | አንቀጽ መጻፍ | 1 |
| 7 | ምሳሌያዊ አባባሎችን በጽሁፍ መግለጽ፣ የቃላትን የፍቺ ልዩነት መጻፍ፣ስርዓተነጥቦችን መጻፍ፣ | 1 |
| 8 | አሰረጂ ድርሰት መጻፍ | 1 |
| 9 | አባባሎችን መጻፍ፣ አንቀጽመጻፍ፣ደበዳቤ መጻፍ፣ | 1.5 |
| 10 | ድርሰት መጻፍ | 1 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለጽህፈት ክሂል ትምህርት የተሰጣውን ሽፋን ነው፡፡በአመት ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በጠቅላላው ከተመደበው ሰባ ስድስት ክፍለጊዜ ውስጥ በጽህፈት ክሂል ለመሸፈን የታቀደው ክፍለጊዜ ብዛት 11 ብቻ ሲሆን በነዚህ 11 ክፍለ ጊዜያት በአመቱ ውስጥ ለመተግበር የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ፣ተገቢ ናቸው፣...ወዘተ ተብለው ለትምህርትነት ተመርጠውና ተዘጋጅተው የቀረቡት ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ/ አረፍተ ነገር

አረፍተ ነገር በምዕራፍ አንድና በምዕራፍ ዘጠኝ በይዘትነት ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አንድ፣ ቃላትና ሀረጋትን በክፍት ቦታው ላይ በማስገባት አረፍተነገሮችን አሟልተው መጻፍ በሚል ሲሆን በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ ዘይቤያዊ ቃላትና ሀረጋትን በአረፍተነገር ውስጥ አስገብተው ይጽፋሉ የሚሉ ናቸው፡፡

### ለ/አንቀጽ መጻፍ

አንቀጽ በሶስት ምዕራፎች ማለትም በምዕራፍ አንድ፣ በምዕራፍ ስድስትና በምዕራፍ ዘጠኝ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አንድ፣ የተሟላ አንቀጽ ይጽፋሉ፤በምዕራፍ ስድስት ደግሞ የቀረበውን ቢጋር መሰረት በማድረግ አንቀጽ ይጽፋሉ እና የአረፍተነገሮችን ቅደምተከተሎች በማስተካከል አንቀጽ ይጽፋሉ የሚሉ ናቸው፡፡

### ሐ/ ድርሰት መጻፍ

ድርሰት በመርሃ ትምህርቱ በስፋት የተተኮረበት ይዘት ሆኗል፡፡ በአምስት ምዕራፎች ስለድርሰት መጻፍ የሚናገሩ ርዕሶች አሉ፡፡እነዚህም ምዕራፍ ሁለት፣ ሶስት፣ አምስት፣ ስምንትና አስር ናቸው፡፡በምእራፍ ሁለት፣ ገላጭ ድርሰት ይጽፋሉ፤ በምዕራፍ ሶስት፣ ርዕስ መርጠው አስረጂ ድርሰት ይጽፋሉ፤ በምዕራፍ አምስት፣ ገላጭ ድርሰት ይጽፋሉ፤በምዕራፍ ስምንት፣ ባለእጆች በሚሰሩት የዕደጥበብ ውጤት ላይ በመመስረት አስረጂ ድርሰት ይጽፋሉ፤ እንዲሁም በምዕራፍ አስር፣ ሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን መሰረት በማድረግ ድርሰት (አይነቱ አልተገለጸም) ይጽፋሉ የሚሉ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በቀጥታ ድርሰት በሚል ባይቀርቡም ድርሰት ነክ የሆኑ ሁለት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ተካተዋል፡፡ እነዚህም ደብዳቤና ዘገባ ናቸው፡፡ ደብዳቤን በሚመለከት በምዕራፍ ዘጠኝ "ደብዳቤ ይጽፋሉ" በሚል የቀረበ ሲሆን ዘገባ ደግሞ በምዕራፍ አራት "በተመለከቱት ትዕይንት ላይ ተመስርተው ዘገባ ይጽፋሉ" በሚል ቀርቧል፡፡ ዘገባና ደብዳቤ በአቀራረባቸው ከአረፍተ ነገርና ከአንቀጽ የተለዩ ስለሆኑ በድርሰት ስር ተካተው ቀርበዋል፡፡

### መ/ አባባሎችን በጽሁፍ ማብራራት

አባባሎችን በጽሁፍ ስለማብራራት በሁለት ምዕራፎች ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ስለሴቶች

የሚነገሩ አባባሎችን ያብራራሉ፤ እንዲሁም በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ አባባሎችን በጽሁፍ ይገልጻሉ የሚሉ ናቸው፡፡

### ሠ/ የቃላትን ትርጉም መጻፍ

የቃላትን ትርጉም በጽሁፍ ማሳየትን በሚመለከት የቀረበው በምዕራፍ ሰባት ብቻ ነው፡፡ አቀራረቡም በቃላት መካከል የሚታየውን የፍቺ ልዩነት በጽሁፍ ይገልጻሉ የሚል ነው፡፡

### ረ/ የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም

የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም በምዕራፍ ሰባት "የስርዓተ ነጥቦችን ጠቀሜታ ይለያሉ" በሚል ቀርቧል፡፡(እነዚህ ከሀ-ረ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ከተማሪው መጽሀፍ ይዘቶች ጋር ባንድ ላይ ሆነው ክብደት ቀላልነታቸው፣ተገቢነታቸውና ትክክለኛ ቅደም ተከተል ይዘው መዘጋጀታቸው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡) ከላይ ሠንጠረዥ 4ን መሰረት በማድረግ በቀረበው ማብራሪያ መሰረት እያንዳንዱ የጽህፈት ክሂል ይዘት ወይም መልመጃ ከሌላው አንጻር የያዘው ስፋት ወይም ሽፋን እንደሚከተለው በመቶኛ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 5፡-</u> የ9ኛ ክፍል አማርኛ መርሃትምህርት ውስጥ ያለውን የጽህፈት ክሂል ይዘት የስርጭት ሽፋን

| በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተተው የጽህፈት ክሂል ይዘት ዝርዝር | ይዘቱ የተገኘባቸው ምዕራፎች ብዛት (ድግግሞሽ ብዛት) | ከጠቅላላው የጽህፈት ክሂል የያዘው ሽፋን በ% |
|---|---|---|
| አረፍተ ነገርን መጻፍ | 2 | 12.5 |
| አንቀጽ መጻፍ | 3 | 18.75 |
| ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ዘገባ መጻፍ | 7 | 43.75 |
| አባባሎችን ማብራራት | 2 | 12.5 |
| የቃላትን ትርጉም መጻፍ | 1 | 6.25 |
| የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም | 1 | 6.25 |
| ድምር | 17 | 100 |

ይህ ሠንጠረዥ የያዘው መረጃ የሚያሳየው በ2014ዓ.ም. በታተመው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መርሃትምህርት ውስጥ ላለው የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘት የተሰጠውን ሽፋን ነው፡፡

በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ በጣም ሰፊ ትኩረት የተሰጠው ለድርሰትና ለድርሰት ነክ ጽሁፍ(ደብዳቤ እና ዘገባ) ነው፡፡ለዚህ ይዘት ለጽህፈት ከተመደበው ጊዜ 43.75 በመቶው ተመድቧል፡፡ አንቀጽ 18.75 በመቶውን ሽፋን በመያዝ ድርሰትን በርቀት ይከተላል፡፡በቀጣይነት 12.5 በመቶ እያንዳንዳቸው በተላይ በመሸፈን አንቀጽን የተከተሉት አረፍተነገሮችን መመስረትና ምሳሌያዊ አባባሎችን ማብራራት ናቸው፡፡ የቀሩት ሁለቱ ማለትም የቃላትን ትርጉም መጻፍና የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም አነስተኛ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡እያንዳንዳቸው 6.25 በመቶውን እንዲይዙ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የሚያሳየው በ2014 ዓ ም የታተመው መርሀ ትምህርት ለድርሰትና ድርሰት ነክ ለሆኑ የጽህፈት ተግባራት ሰፊ ሽፋን ሰጥቶ መዘጋጀቱን ነው፡፡አንቀጽ መጻፍ፣ አረፍተነገሮችን መመስረት፣ አባባሎችን በጽሁፍ ማብራራት፣ ለቃላት በጽሁፍ ትርጉም መስጠትና የስርኣተነጥቦችን አጠቃቀም መግለጽ ከሰፊ ወደ ጠባብ ሽፋን በቅደም ተከተላቸው መሰረት እንዲይዙ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

ባጠቃላይ በ2014ዓ.ም.ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ውስጥ ለጽህፈት ክሂል ማስተማሪያነት የቀረቡት ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

* ድርሰት መጻፍ
* አንቀጽ መጻፍ
* አረፍተነገሮችን ማዋቀር
* አባባሎችን በጽሁፍ ማብራራት
* ደብዳቤ መጻፍ
* ዘገባ መጻፍ
* የቃላትን ትርጉም ማብራራትና
* የስርኣተ ነጥቦችን አጠቃቀም በጽሁፍ ማሳየት ናቸው፡፡(ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን የሚገልጸው ማብራሪያ ከታች ከተማሪው መጽሐፍ ከተገኙ ይዘቶች ጋር አብሮ ቀርቧል፡፡)

### 4.1.4. በ2014 ዓ. ም.በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌደራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለማስተማሪያነት የቀረቡ ይዘቶች

ይህ አጥኚ ለጥናቱ የመረጠው መጽሀፍ የ2014 ዓ ም ህትመት ውጤት የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ መጽሀፉ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍም በስድስት ክፍሎች የክሂልና የዕውቀት ዘርፎችን ለማስተማር የሚመች

በሚመስል መልኩ ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ ከነዚህ የተለየ “ክፍል ሰባት፣ የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች” በሚል የተዘጋጀ ቢኖርም ማስተማሪያ ስላልሆነ በጥናቱ አልተካተተም፡፡ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱን ምዕራፍ በክሂልና ዕውቀት ዘርፎች ከፋፍሎ ለማስተማር የተደራጁት ክፍሎች ተፈጥሯዊውን የቋንቋ ለመዳ ሂደት የተከተለ እንደሆነ ተገልጿል፡፡በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ማለትም የተማሪው መጽሀፍና መርሀ ትምህርት ከአንድ እስከ ሶስት ያሉት ክፍሎች (ማዳመጥ፣ መናገርና ማንበብ) በተመሳሳይ ቅደምተከተል ተደራጅተዋል፡፡ክፍል አራትና አምስት በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ቦታ ተለዋውጠው ተቀምጠዋል፡፡የመርሀ ትምህርቱ ክፍል አራት የጽህፈት ክሂልን ርዕሰ ጉዳይ የያዘ ሲሆን የተማሪው ክፍል አራት ግን የቃላት ትምህርትን ይዘት ቀርጾ ቀርቧል፡፡ክፍል ስድስት በሁለቱም በተመሳሳይ ቦታ ነው ያለው፡፡ተፍጥሯዊው የቋንቋ ለመዳ ሂደት መዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣መጻፍ...እያለ የሚሄድ መሆኑ ትክክል ከሆነ የመርሀ ትምህርቱ የርዕሰ ጉዳዮች አደረጃጀት ትክክለኛ አደረጃጀት ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል በመርሀ ትምህርቱ ምዕራፍ ዘጠኝ ክፍል ስድስት የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ በተቀሩት ዘጠኙም ምዕራፎች ቀርቦ የነበረው ሰዋሰው ሳይሆን ስነጽሁፍ ነው፡፡ሆኖም በተማሪው መጽሀፍ የአስሩም ምዕራፎች ክፍል ስድስት በተመሳሳይ መልኩ ሰዋሰው ሆኖ ቀርቧል፡፡በዚህ መሰረት ስድስቱም ይዘቶች እያንዳንዳቸው ከመቅላላ የመጽሀፉ ይዘቶች 16.66 በመቶውን በመሸፈን ተመጣጣኝ የይዘት ስርጭት ሽፋን በመያዝ ተደራጅተዋል፡፡

### 4.1.5.የ2014 ዓ ም ህትመት የ9ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የመጻፍ ትምህርት ይዘት

ከላይ በቀረቡት ክፍሎች ለማሳየት እንደተሞከረው የመጻፍ ክሂል ይዘት በአስሩም ምዕራፎች፣በክፍል አምስት ስር ተሰራጭቶ ይገኛል፡፡በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ በየምዕራፉ ያለው የጽህፈት ክሂል ይዘት ርዕሶች መጠንና አይነት የተለያየ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል ይዘትና ርዕሰ ጉዳዮች አቀራረብና አደረጃጀት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል

ሠንጠረዥ 6. የ9ኛ ክፍል አማርኛ መጽሀፍ የቀረበው የመጻፍ ክሂል ይዘት ስርጭት

| ምዕራፍ | የጽህፈት ክሂል ይዘት መልመጃዎች | የተሰጠው ሽፋን |
|---|---|---|
| 1 | -ክፍት ቦታዎችን በመሙላት አረፍተነገሮችን መጻፍ | አንድ ርዕስ |
| 2 | -አንቀጽ መጻፍ፣-አባባሎችን መጻፍ | ሁለት ርዕሶች |
| 3 | -አንቀጽ መጻፍ | አንድ ርዕስ |
| 4 | -ዘገባ መጻፍ | አንድ ርዕስ |
| 5 | ...በጽሁፍ መግለጽ (የጽሁፉ አይነት ያልተገለጸ) | አንድ ርዕስ |
| 6 | -ድርሰት መጻፍ | አንድ ርዕስ |
| 7 | -ለቃላት ፍቺ መጻፍ፣-ተቀራራቢ ትርጉም ባላቸው ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት በአረፍተነገር ማሳየት፣ስርኣተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጻፍ | ሶስት ርዕሶች |
| 8 | የግብርና የቀረጥን ልዩነት መጻፍ፣-የግብር አይነትና ደረጃዎችን በጽሁፍ መግለጽ (የጽሁፉ አይነት ያልተገለጸ) | ሁለት ርዕሶች |
| 9 | -...በራስ አባባል መጻፍ፣ አንቀጽን ሙሉ ማድረግ፣ አንቀጽ መጻፍ፣ ደብዳቤ መጻፍ | አራት ርዕሶች |
| 10 | የግለሰብን ስራ በጽሁፍ መግለጽ (አይነቱ ያልተለየ ጽሁፍ) | አንድ ርዕስ |
| | የርዕስ ጉዳዮች ድምር | 17 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያሳየው በ2014 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡትን የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀትና ስርጭትን ነው፡፡የይዘቶቹ ትኩረት በአብዘኛው አንቀጽና ድርሰት መጻፍ ላይ ነው፡፡ይህም መሆን ያለበት የዚህ ዝግጅት ጠንካራ ጎን ነው፡፡ከላይ በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቆመው በትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ወቅት በሚፈጸሙ ስህተቶችና ትኩረት ማጣት የመጻፍ ተግብር በትላልቅ መገናኛ ብዙሃን እንኳን ሳይቀር ትኩረት እያጣና እየወደቀ

ለመጻፍ ስራ ትክክለኛነት ግድየለሽነት ስር እየሰደደ መጥቷል፡፡ስለዚህ በትምህርትነት መጻፍንን በተላይም አንቀጽና ድርሰት መጻፍን ትኩረት ያደረጉ መልመጃዎችን ትኩረት ሰጥቶ ማብዛት ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ በምዕራፍ አንድና ሰባት አረፍተ ነገርን በተመለከተ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳይና መልመጃዎች በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ መቅረብ ያለባቸው ይዘቶች ናቸው የሚል እምነት አይኖርም፡፡ቢያንስ ከሶስተኛ ወይም ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ አማርኛን ለተማረ ተማሪ በዚህ ክፍል አረፍተ ነገር ማዋቀርን ማቅረቢ ተገቢ አይመስለኝም፡፡

በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች በምዕራፍ ሰባት ስር ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ ስለመጠቀም የቀረቡት ርዕሰጉዳይና መልመጃ ከተገቢነትም ሆነ ከቅደምተከተል አንጻር ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ይመስላል፡፡ ከቅደምተከተል አንጻር ተማሪዎች በርካታ አንቀጽና ድርሰቶችን እንዲጽፉ ከመታዘዛቸው በፊት ስርዓተ ነጥቦችን የትና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የሚሳዩ ትምህርቶቸ በቀዳሚ ምዕራፎች መቅረብ ነበረባቸው፡፡ ከተገቢነት አንጻርም ውስብስብ ከሆኑ እንደ ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ካሉት ስርዓተ ነጥቦች ውጪ የቀረቡት ስርዓተ ነጥቦች በቀደሙት የክፍል ደረጃዎች በስፋት የቀረቡ ስለሆነ ለዚህ ክፍል ይመጥናሉ፤ተገቢ ናቸው የሚል እምነት የለኝም፡፡

ባጠቃላይ የአንቀጽና የድርሰት በተለያዩ ምዕራፎች በተደጋጋሚ መምጣት የጽህፈት ክሂልን መውደቅ ከግምት ያስገባ ዝግጅት ስለሆነ ተጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡ከዚህ አንጻር መርሀ ትምህርቱና የተማሪው መጽሀፍ ተጣጥመው ተዘጋጅተዋል፡፡በአንጻሩ በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች የአረፍተነገር መዋቅር ተገቢነቱ አስገዳጅ ያልሆነ፣የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም መልመጃ ደግሞ ከቅደምተከተልም ሆነ ከተገቢነት አንጻር መስተካከል ያለበት ዝግጅት ነው፡፡

ከላይ የቀረቡት፣ በዘጠነኛ ክፍል የተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙት አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ያገኙት ትኩረትና ለትምህርትነት የቀረቡት መልመጃዎች ባጠቃላይ የተሰጣቸው የርዕስና የይዘት ሽፋን በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

<u>ሠንጠረዥ</u>7፡- የአዲሱ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የጽህፈት ክሂል ይዘት የስርጭት ሽፋን

| ተ.ቁ | በአዲሱ የ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ትኩረት ያገኙ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች | ይዘቱ ያለበት ምዕራፍ/ምዕራፎች | የርዕሶች ብዛት | ይዘቱ ሽፋን በ% |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላትን ትርጉም መጻፍ | ምዕራፍ 7 | 2 | 11.8 |
| 2 | ስርዓተ ነጥቦችን መጻፍ | ምዕራፍ 7 | 1 | 5.9 |
| 3 | አረፍተ ነገርን ማዋቀር | ምዕራፍ 1 | 1 | 5.9 |
| 4 | አንቀጽ መጻፍ | ምዕራፍ 2፣3፣9 | 4 | 23.45 |
| 5 | ድርሰት መጻፍ | ምዕራፍ 6 | 1 | 5.9 |
| 6 | ምሳሌያዊ አባባሎችን መጻፍ | ምዕራፍ 2 | 1 | 5.9 |
| 7 | ደብዳቤ መጻፍ | ምዕራፍ 9 | 1 | 5.9 |
| 8 | ዘገባ መጻፍ | ምዕራፍ 4 | 1 | 5.9 |
| 9 | “በጽሁፍ ግለጹ” ወይም ”ጻፉ” በሚል የቀረቡ መልመጃዎች | ምዕራፍ 5፣ 8፣ 9፣ 10 | 5 | 29.5 |
| | ድምር | | 17 | 100 |

ይህ ሠንጠረዥ የሚያሳየው አዲስ በ2014 በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በ2015 በሙካራ ትግበራ ላይ ባለው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ለጽህፈት ክሂል የሰጠውን ትኩረት ነው፡፡ ሰፊ የጽህፈት ሽፋን የተሰጠው ክፍል “ጻፉ” ወይም “በጽሁፍ ግለጹ” የሚል ሆኖ 29.5 በመቶውን የጽህፈት ድርሻ ሸፍኗል፡፡ በመቀጠል 23.45 በመቶውን የጽህፈት ድርሻ የያዘው ደግሞ አንቀጽ መጻፍ ነው፡፡ የቃላትን ትርጉም መጻፍ ፣ከአንቀጽ መጻፍ በግማሽ ቀንሶ 11.8 በመቶ ድርሻ ሸፍኗል፡፡የቀሩት ስድስቱ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ አረፍተ ነገርን ማዋቀር፣ ድርሰት መጻፍ፣ ምሳሌያዊ አባባሎችን መጻፍ፣ ደብዳቤ መጻፍ እና ዘገባ መጻፍ እያንዳንዳቸው በአንድ በአንድ ርዕሰ ጉዳዮች በመወከል በየግላቸው 5.9 በመቶ፣ ስድስቱም በጋራ የጽህፈትን ክሂል 35.1 በመቶ ድርሻ ሸፍነዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ከመጽሀፉ የጽህፈት ክሂል ድርሻ ወደ ሰድሳ አምስት በመቶ የሚጠጋው ከአረፍተ ነገር በላይ በሆኑ ጽሁፎች መሸፈኑን ነው፡፡

በጠቃላይ በ2015 ዓ ም በኢትዮጵያ በጥቂት ትምህርት ቤቶች በሙካራ ትግበራ ስራ ላይ የሚገኘው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ የተማሪው መጽሀፍ፣ የውጪው ሽፋን በኣብዛኛው አረንጓዴ ቀለም ያለው፣ ክሂሎችን በሚያሳይ ስዕል ያጌጠ፣

የትምህርት ሚኒስቴር አርማ ያለበት ነው። ወደ ውስጥ ሲገባም ለመጽሀፉ ተጠቃሚዎች የሚሆን የጥንቃቄ መልዕክት የያዘ ገጽ፣ የመጽሀፉ ዝግጅት ክፍል አባለትን የሚጠቁም ገጽ፣የምስጋናና የይዘት ማውጫ ገጾች ይገኛሉ። በመቀጠል የመግቢያ ክፍሉ የመጽሀፉን ሁኔታ ባጭሩ ያስቃኘ ሲሆን የመጽሀፉ የይዘት አደረጃጀትም ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳ ሂደትን መሰረት ያደረገ እንደሆነ በመጠቆም ቅደም ተከተሉንም ማዳመጥ፣ ንግግር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ጽህፈትና ሰዋሰው አድርጎ አስቀምጧል።

### 4.1.6. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የመጻፍ ክሂል ይዘት ለክፍሉ ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ርዕሰ ጉዳዮች ጋር ያለው መጣጣም

በተማሪው መጽሀፍ ስፋት አግኝተው በመልመጃ መልክ ሊቀርቡ የሚችሉ ይዘቶች ሁሉ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በጥቂቱ መጠቆም ያለባቸው መሆኑ ግዴታ ነው።ይህ ጥናት ሊፈትሽ የተነሳውም ይህንኑ ነው።ከዚህ መሰረታዊ ሀሳብ በመነሳት የ2014 ዓ.ም.ዝግጅት ሆነው በ2015 ዓ.ም ለሙካራ ትግበራ ላይ ባሉት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በአስሩም ምዕራፎች፣በመርሀ ትምህርቱ ተጠቁመው በተማሪው መጽሀፍ እነዚሁ የተጠቆሙት ይዘቶች ሳይለወጡ ስፋት አግኝተው በመልመጃ መልክ መቅረብ አለመቅረባቸው በሚከተለው ሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል።

**<u>ሰንጠረዥ 8፡-</u> የጽህፈት ክሂል ይዘት ስርጭት በ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መጽሀፍና በመርሀ ትምህርት መካከል ያለው የመጻፍ ክሂል ተጣጥሞሽ**

| *ምዕራፍ* | *በመርሀ ትምህርቱ የተጠቆመው የጽህፈት ክሂል ርዕሶች* | *በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች* |
|---|---|---|
| 1 | • አንቀጽ መጻፍ • ክፍት ቦታዎችን መሙላት | ¤ የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ…በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በጽሁፍ አሟሉ። |
| 2 | • ገላጭ ድርሰት መጻፍ •የአባባሎችን ምንነት መጻፍ | ¤ ለማህበረሰቡ አርኣያ በመሆን ከሚታወቁ ሴቶች መካከል አንድ በመምረጥ አርኣያ ስለሆኑበት ጉዳይ ገላጭ አንቀጽ ጻፉ። ¤ ከሴቶች ጋር በተያያዘ ከሚነገሩ ምሳሌያዊ አባባሎች አምስት ጻፉ። |
| 3 | •ድርሰት መጻፍ | ¤ ከታች ከተዘረዘሩት፣ የቴክኖሎጂ ውጤት ከሆኑት መሳሪያዎች መካከል አንዱን በመምረጥ ጥቅምና አሰራሩን የሚገልጽ አንቀጽ ጻፉ። |
| 4 | •ዘገባ መጻፍ | ¤…የኮሮናን የውጥረት ጊዜ እንዴት እንዳሳለፋችሁትና ምን ተሰምቷችሁ እንደነበር የሚያሳይ ዘገባ ጻፉ። |
| 5 | •ገላጭ ድርሰት መጻፍ | ¤ የኦቲዝም በሽታን ምንነትና ባህሪ በሚመለከት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በጽሁፍ ግለጹ። |
| 6 | •አንቀጽ መጻፍ | ¤ በሀገራችን ከሚገኙት አራት ወቅቶች መካከል አንዱን በመምረጥ የወቅቱን ትክክለኛ ባህሪ የሚያሳይ መግቢያ፣ሀተታና መደምደሚያ ያለው ድርሰት ጻፉ። |
| 7 | •አባባሎችን በጽሁፍ መግለጽ •የቃላትን ልዩነት በጽሁፍ ማብራራት •ስርዓተ ነጥብ | ¤ ቀጥሎ ለተሰመረባቸው አባባሎች …ፍቺ በጽሁፍ ስጡ። ¤ በሚከተሉት ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት አረፍተ ነገር በመስራት አሳዩ። ¤ ስርኣተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ። ¤በአካባቢያችሁ የሚገኙ ወጣቶች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱን በመምረጥ ገላጭ ድርሰት ጻፉ። |
| 8 | •አስረጂ ድርሰት መጻፍ | ¤ በግብርና በቀረጥ መካከል ያለውን ልዩነት በጽሁፍ አብራርታችሁ ግለጹ። ¤…ስንት የግብር አይነትና ደረጃዎች እንዳሉና እንዴት እንደሚተገበሩ አብራርታችሁ በጽሁፍ ግለጹ። |
| 9 | •አባባሎችን በጽሁፍ ማብራራት •የዘይቤ ምንነትና አይነቶችን መጻፍ •ደብዳቤ መጻፍ •የቃላትን አገባባዊ ፍቺ መጻፍ | ¤ የሚከተሉት ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አብራርታችሁ ጻፉ። ¤…ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል በመምረጥ በምንባቡ ውስጥ ክፍት በተተው ቦታዎች በማስገባት አንቀጹን አስተካክላችሁ ጻፉ። ¤ ከዚህ ቀጥሎ ቅደምተከተላቸው ተዘበራርቆ የተቀመጡትን አረፍተነገሮች በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ። ¤…በቡድን ሆናችሁ ያነበባችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ለጓደኛችሁ ደብዳቤ ጻፉ። |
| 10 | •ድርሰት መጻፍ | ¤…በአካባቢያችሁ ማህበረሰብን ሊጠቅም በሚችል ስራ ብዙ ከደከሙና ጉልህ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል አንዱን/ዷን በመምረጥ…ስራውን/ዋን በጽሁፍ ግለጹ። |

ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት ያደረገው የ9ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍና ለክፍሉ በተዘጋጀው መርሀትምህርት መካከል ያለውን የጽህፈት ክሂል ይዘት

አቀራረብና የመልመጃዎችን አደረጃጀት ተጣጥሞሽ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ በሰንጠረዥ 8 ተተንትኖ የቀረበው አጠቃላይ መረጃ በየምዕራፉ ያለው የተጣጣሚነት ሁኔታ እንደሚከተለው ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

በምዕራፍ አንድ መርሀ ትምህርቱ ሁለት ይዘቶችን ጠቁሟል፡፡ ይዘቶቹም 1ኛ.አንቀጽ መጻፍ 2ኛ.ክፍት ቦታዎችን መሙላት ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደረጃ የተማሪው መጽሀፍ እንደ መርሀ ትምህርቱ ሁሉ ክፍት ቦታዎችን በመሙላት አረፍተ ነገሮችን ሙሉ አድርጎ ስለመጻፍ የቀረበ መልመጃ አለው፡፡ አንቀጽን በተመለከተ የቀረበ መልመጃ የለም፡፡ይህ የሚያሳየው በመርሀ ትምህርቱ በይዘትነት የቀረበው አንቀጽ በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በመልመጃዎች አለመደገሙ በዚህ ምዕራፍ ደረጃ የጽህፈት ክኂልን በሚመለከት በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የይዘት ተጣጥሞሽ መኖሩን ነው፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ በመርሀ ትምህርት ተካተው የቀረቡት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ሁለት ናቸው፡፡እነዚህም 1ኛ ምሳሌያዊ አባባሎች አብራርቶ መጻፍን የሚመለከት፣ 2ኛ ገላጭ ድርሰት መጻፍ የሚሉ ናቸው፡፡ በአንጻሩ በዚሁ ምዕራፍ በተማሪው አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙት ሁለት መልመጃዎች 1ኛ ገላጭ አንቀጽ ጻፉ የሚል ሲሆን 2ኛው… ምሳሌያዊ አባባሎችን ማብራራት የሚመለከት ነው፡፡ ከላይ በምዕራፍ አንድ እንደታየው በዚህኛውም ምዕራፍ አንደኛው ይዘት በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች በተመሳሳይ መልኩ የቀረበ ሲሆን ሁለተኛው ይዘት ግን በሁለቱም የተለያየ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ገላጭ ድርሰት መጻፍን የሚመለከት ይዘት የተጠቆመ ሲሆን በአንጻሩ በተማሪው መጽሀፍ የቀረበው የጽህፈት ክሂል መልመጃ ግን ገላጭ አንቀጽ መጻፍን የሚመለከት ነው፡፡ ገላጭ የመሆን ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም አንቀጽና ድርሰት ግን በባህርይም ሆነ በመጠን የተለያዩ ናቸው፡፡ስለዚህ ይህ በሁለተኛውም ምዕራፍ የይዘት ተጣጣሚነት ችግር እንዳለ ማሳያ ነው፡፡

የምዕራፍ ሶስት ይዘት በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በተማሪው መጽሀፍ ተመጣጣኝ ነው፡፡ አንድ ይዘት ቀርቧል፡፡ በመርሀ ትምህርቱ የቀረበው ድርሰት መጻፍ የሚል ይዘት ሆኖ በተማሪው መጽሀፍ የቀረበው ግን… አንቀጽ ጻፉ የሚል ነው፡፡ እዚህም በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች የቀረበው የጽህፈት ክሂል ይዘትና መልመጃው የተለያዩ ስለሆኑ በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ መካከል የተጣጣሚነት ችግር አለ ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ አራት ዘገባ ስለመጻፍ የሚገልጽ ይዘትና መልመጃ የቀረበበት ምዕራፍ ነው፡፡ዘገባ መጻፍ በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በመልመጃ መልክ

ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህኛው ምዕራፍ የጽህፈት ክሂል የተጣጣሚነት ችግር በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች መካከል የለም፡፡

የምዕራፍ አምስት በመርሀ ትምህርቱ የተጠቀመው ይዘት ገላጭ ድርሰት መጻፍ የሚል ነው፡፡በተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለጽህፈት ክሂል መልመጃነት የቀረበው ይዘት… በጽሁፍ ግለጹ የሚል ሆኖ ቀርቧል፡፡ እዚህ ላይ በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች መካከል የሚታየው ልዩነት መርሀ ትምህርቱ ገላጭ ድርሰት መጻፍን የሚጠቁም ሲሆን የተማሪ መጽሀፉ የጽህፈት ክሂል መልመጃ ትዕዛዙ አንቀጽ ይሁን ድርሰት ተለይቶ አልቀረበም፡፡ በደፈናው ‹‹በጽሁፍ ግለጹ›› በሚል ቀርቧል፡፡ ገላጭ ድርሰት መጻፍ በሚል ይዘትና በጽሁፍ ግለጹ በሚል መልመጃ መካከል ልዩነት አለ፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥም በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መጽሀፍ በቀረበው መልመጃ መካከል በጣም አስቸጋሪ ባይሆንም የተጣጣሚነት ችግር አለ ማለት ነው፡፡ ተማሪው ምን ልጻፍ ቢል አይኮነንም፡፡ ተለይቶ የተሰጠው ግልጽ ነገር የለምና፡፡

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ በመርሀ ትምህርት ደረጃ አንቀጽ መጻፍ የሚል የጽህፈት ክሂል ይዘት ተጠቁሟል፡፡ ይህን ይዘት ለማስረጽ በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ ተዘጋጅቶ የቀረበው መልመጃ ግን ድርሰት ጻፉ የሚል ነው፡፡ከላይ በአብዛኞቹ ምዕራፎች እንደታየው ሁሉ አንቀጽ እና ድርሰት የተለያዩ ስለሆኑ እዚህ ምዕራፍ ውስጥም የጽህፈት ክሂል ይዘትና የመልመጃው አለመጣጣም አለ ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ ሰባት ከላይ ካየናቸው ማዕራፎች በተለየ መልኩ በርከት ያሉ ይዘቶችን ያካተተ ምዕራፍ ነው፡፡ይዘቶቹም 1ኛ አባባሎችን በጽሁፍ መግለጽ፣ 2ኛ የቃላትን ልዩነት በጽሁፍ ማብራራትና 3ኛ ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጻፍ የሚሉ ሲሆኑ በተማሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ደግሞ አራት ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ሶስቱ ሙሉ በሙሉ መርሀ ትምህርቱ ውስጥ ስለተጠቀሙ ከላይ ከ1ኛ እስከ 3ኛ በዝርዝር ከቀረቡት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ በመልመጃነት ቀርቦ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ግን በይዘትነት ያልቀረበው መልመጃ "በቡድን ገላጭ ድርሰት ጻፉ" የሚል ነው፡፡ ይህ በተማሪው መጽሀፍ በሰባተኛው ምዕራፍ አራተኛው የጽህፈት ክሂል መልመጃ ሆኖ የቀረበው ገላጭ ድርሰት የመጻፍ መልመጃ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በይዘትነት ያልተጠቀመ በመሆኑ በዚህም ምዕራፍ በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ መካከል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በይዘት ያለመጣጣም ችግር አለ ማለት ይቻላል፡፡ምክንያቱም በዚህ ምዕራፍ ድርሰት ስለመጻፍ የቀረበ ርዕስ የለም፡፡

በስምንተኛው ምዕራፍ የክፍሉ መርሀ ትምህርት አንድ ይዘት ብቻ አቅርቧል፡፡ይዘቱም "አስረጂ ድርሰት መጻፍ" የሚል ነው፡፡ በዚሁ ምዕራፍ በተማሪው መጽሀፍ ግን ሁለት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡እነዚህም 1ኛ በግብርና በቀረጥ መካከል ያለውን ልዩነት በጽሁፍ አብራርታችሁ ግለጹ የሚል ሲሆን 2ኛው …በሀገራችን ስንት የግብር አይነቶች እንዳሉ፣ እንዲሁም ስንት የግብር ደረጃዎች እንደሚተገበሩ መጽሀፍ በማንበብ ወይም የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ አብራርታችሁ በጽሁፍ ግለጹ፡፡ በዚህ ምዕራፍ መርሀ ትምህርቱ አስረጂ ድርሰት መጻፍን በጽህፈት ክሂል ይዘትነት ያቀረበ ሲሆን የተማሪው መጽሀፍ ግን "አብራርታችሁ በጽሁፍ ግለጹ"በማለት አስቀምጧል፡፡በጽሁፍ ግለጹ ሲል ጽሁፉ አንቀጽ ይሁን ድርሰት ተለይቶ አልቀረበም፡፡ሆኖም በዚህ ምዕራፍ በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች በቀረቡ የጽህፈት መካከል የብዛት ልዩነት ያለ ቢሆንም የጽህፈት ክሂል መሆናቸው ግን የሰፋ የተጣጣሚነት ችግር የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ እንደ ምእራፍ ሰባት በርከት ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘትና መልመጃዎችን ያከተተ ምዕራፍ ነው፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት አራት ይዘቶች ናቸው፡፡ እነዚህም 1ኛ የዘይቤ ምንነትና አይነቶችን መጻፍ፣ 2ኛ አባባሎችን በጽሁፍ መግለጽ፣ 3ኛ ደብዳቤ መጻፍና 4ኛ የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው መለየት የሚሉ ናቸው፡፡ በተማሪው መጽሀፍ በመልመጃነት የቀረቡትም ይዘቶች በቁጥር አራት ናቸው፡፡ 1ኛ… ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በራስ አገላለጽ አብራርቶ መጻፍ፡፡ 2ኛቃላትን በምንባቡ ውስጥ በተተውት ባዶ ቦታዎች ውስጥ በማስገባት አንቀጽን አስተካክሎ መጻፍ፡፡ 3ኛ …ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ የተቀመጡትን አረፍተ ነገሮች በማስተካከል አንቀጽ መጻፍ፡፡ 4ኛ ያነበባችሁትን ጽሁፍ መነሻ በማድረግ ለጓደኛ ደብዳቤ መጻፍ፡፡ በዚህኛው ምዕራፍ መርሀ ትምህርቱና የተማሪው መጽሀፍ "…ለጓደኛችሁ ደብዳቤ ጻፉ" በሚል ይዘት ብቻ ተመሳሳይ ሆነው በሌሎቹ በሶስቱም ፍጹም ተለያይተዋል፡፡ ለምሳሌ የዘይቤ ምንነትና ዓይነቶች፣ አባባሎችን በጽሁፍ መግለጽና የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው መለየት፣ በመርሀ ትምህርቱ ያሉ በተማሪው መጽሀፍ ግን የሌሉ ናቸው፡፡በአንጻሩ በተማሪው መጽሀፍ በ1ኛ፣ በ2ኛና በ3ኛ ተራ ቁጥሮች ለተማሪዎች የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በጽህፈት ክሂል ይዘትነት ያልቀረቡ ናቸው፡፡ሁሉም የጽህፈት ይዘቶች ቢሆኑም በትይዩ ቢገጣጠሙ ይመረጣል፡፡

ምዕራፍ አስር በመርሀ ትምህርት ደረጃ የያዘው የጽህፈት ክሂል ይዘት"ድርሰት መጻፍ" የሚል ሲሆን የተማሪው አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በመልመጃነት ይዞ የቀረበው "…በአካባቢያችሁ ማህበረሰብን ሊጠቅም በሚችል ስራ ብዙ ከደከሙና ጉልህ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል አንዱን/ዷን በመምረጥ ባለታሪኩን/ኳን ወይም ሌሎች ሰዎችን

በመጠየቅ ስራውን/ዋን በጽሁፍ ግለጹ" ይላል፡፡መርህ ትምህርቱ "ድርሰት መጻፍ" በሚል ላቀረበው የተማሪው መጽሀፍ "…ስራውን/ዋን በጽሁፍ ግለጹ" የሚል መልመጃ ይዟል፡፡ድርሰት መጻፍና በጽሁፍ ግለጹ የሚሉ ሀሳቦች ቃል በቃል ትይዩ ባይሆኑም ሁለቱም ጽህፈት መሆናቸው ያለመጣጣምን ሁኔታ የጠበበ ያደርጋል፡፡

## 4.2 ከቃለ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

ከላይ በምዕራፍ ሶስት ለመግለጽ እንደተሞከረው ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በከምባታ ጠምባሮ ዞን ደረጃ እየተሞከረ ካለበት በዱራሜ ከተማ ከሚገኝ ህዳሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ከዘጠነኛ ክፍል ሁለት መምህራን፣ ከአስረኛ ክፍል ሁለት መምህራን በድምሩ አራት መምህራንን በመምረጥና በተላይ ለአስረኛ ክፍል መምህራን ከዘጠነኛ ክፍል የጥናቱ ትኩረት የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎች ማለትም የክፍሉን መርህ ትምህርትና የተማሪ መጽሀፍ በ"ሶፍት ኮፒ" አግኝተውና ጊዜ ወስደው በማንበብ እንዲዘጋጁ በማድረግ መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከመምህራኑ የተሰበሰበው መረጃና የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ መምህራኑን በተመለከተ ስማቸው በምዕራፍ ሶስት የቀረበ ስለሆነ በዚህ ትንታኔ መምህራኑ በሆሄ ተወክለው ቀርበዋል፡፡በዚህ መሰረት መምህር ክብሩ ከ9ኛ ክፍል በ"ሀ"፣ መምህርት ትዕግስት ከ9ኛ ክፍል በ"ለ"፣መምህር ደስታ ከ10ኛ ክፍል በ"ሐ"ና መምህርት ዝናሽ ከ10ኛ ክፍል በ"መ" ተወክለዋል፡፡

**ጥያቄ አንድ**፡-ከቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች መካከል መርህ ትምህርት አንዱ ሲሆን በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ስፋት አግኝተው በይዘትነት የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮችን ይጠቁማል፡፡ እርስዎ መርህ ትምህርትን እንደ ትምህርት መሳሪያ የሚጠቀሙት መቼ መቼ ነው?

**"ሀ"** "እኔ መርህ ትምህርትን በትምህርት መሳሪያነት የምጠቀመው በአመታዊ የትምህርት ዝግጅት ወቅት ነው፡፡በውስጡ ለዝርዝር ማስተማሪያነት የሚሆን ዝርዝር ይዘት የሌለው በመሆኑ ሌላ ጊዜ ተመልሼ አላየውም፡፡"

**"ለ"** "እኔ መርህ ትምህርትን፣ከተማሪው መጽሀፍ የማስተማሪያ ዝግጅት ስያዘጋጅ የመምህር መምሪያውን ማየት የማይቀር ስለሆነ በዚሁ አጋጣሚ ለማስተምረው ይዘት የተሰጠውን ትኩረት ለማየት ስል እቃኘዋለሁ፡፡ ሆኖም ስራዬ ብዬ በትኩረት አልመለከተውም፡፡"

**"ሐ"** "መርህ ትምህርት መኖሩን አውቃለሁ፡፡አልፎ አልፎም አነባለሁ፡፡ በተላይ ለማስተማሪያነትም ሆነ ለትምህርት ዝግጅት በሚል ምክንያት አልጠቀምም፡፡ ምክንያቱም ለዝግጅትም ሆነ ለማስተማር በቂ የሆነ ይዘት በስፋት ማግኘት አልችልም፡፡ ጊዜ በከንቱ ማባከን አልፈልግም፡፡"

**"መ"** "እኔ መርሀ ትምህርትን እንደ መነሻ የትምህርት መሳሪያ ስለምመለከት በትኩረት አነባለሁ፡፡በተላይ አመታዊ የትምህርት ዝግጅት ስያዘጋጅ በመምህር እጅ ሊገቡ የሚችሉ ሶስት የትምህርት መሳሪያዎችን ማለትም መርሀ ትምህርት፣ የመምህር መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ በማስተያየት እጠቀማለሁ፡፡"

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከሰጡት መምህራን መካከልሶስት መምህራን ወይም 75%በአንድ ወይም በልላ ምክንያት መርሀ ትምህርትን የሚመለከቱ ሲሆን አንድ መምህር ማለትም 25% መርሀ ትምህርት መኖሩን ከማወቅ ባለፈ እንደማይጠቀም ገልጿል፡፡ ይህ ጥያቄ የቀረበው መምህራን መርሀ ትምህርትን በሚመለከት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ያላቸውን መሰረታዊ መረዳት ለመፈተሽ ስለሆነ ከዚህ በላይ ትንታኔ አይኖረውም፡፡

**ጥያቄ ሁለት፡-**አዲስ በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች በክሂልና ዕውቀት ዘርፎች ሲከፋፈሉ የአከፋፈል ሂደቱ ክፍል አንድ፣ሁለት፣ሶስት፣አራት፣አምስትና ስድስት በሚሉ ክፍሎች ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳና የመማር ሂደታዊ ቅደም ተከተል ይዘው እንደተዘጋጁ በተማሪው መጽሀፍ መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ቅደም ተከተል በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ የተባለውን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል ጠብቀው ተዘጋጅተዋል?

**"ሀ"** አብዛኞቹ የተባለውን ተፈጠሯዊ ቅደም ተከተል ይዘው ሲደራጁ፣ ክፍል አራትና ክፍል አምስት በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መጽሐፍ ቦታ ተለዋውጠዋል፡፡ በመርሀ ትምህርቱ በክፍል አራት የተደራጀው ጽህፈት ሲሆን የተማሪው መጽሐፍ ክፍል አራት ይዘት ቃላት ነው፡፡"

**"ለ"** "ሌሎቹ ርዕሰ ጉዳዮች በተማሪው መጽሐፍ በተጠቀሰው ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል ሲደራጁ ክፍል አራትና ክፍል አምስት በመርሀ ትምህርትና በተማሪው መጽሐፍ ተፈጥሯዊ የተባለውን ቅደም ተከተል አፋልሰዋል፡፡"

**"ሐ"** "ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ተፈጥሯዊ ተብሎ የተቀመጠውን ክፍል በመርሀ ትምህርትና በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ተቀያይረዋል፡፡ ቃላት የሚለው ይዘት በተማሪው መጽሐፍ በክፍል አራት ቀርቧል፡፡ የመርሀ ትምህርቱ ክፍል አራት የያዘው ግን ጽህፈት የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡የአንደኛው ክፍል አራት፣የሌላኛው ክፍል አምስት ነው ማለት ነው፡፡"

**"መ"** "ቃላትና ጽህፈት የተባሉ ርዕሰ ጉዳይና ይዘት በተማሪው መጽሐፍና በመርሀ ትምህርት ቦታቸውን ተለዋውጠው ተቀምጠዋል፡፡"

ለጥያቄ ሁለት ለቃለ መጠይቁ የቀረቡት ሁሉም መምህራን ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ከላይ በክፍል 4.1 ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ በመድገም ሁሉም መምህራን (100%) በመርሀ ትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀትና በተማሪው መጽሐፍ ይዘቶች ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀት መካከል አነስተኛ ሊባል የሚችል መፋለስ አለ በማለት አስቀምጠዋል፡፡መምህራኑ የታየውን የአደረጃጀት ቅደም ተከተላዊ አለመመሳሰል ሲያብራሩም የመርሀ ትምህርቱ ክፍል አራት የሆነው የጽህፈት ክሂል ርዕሰ ጉዳይ፣በተማሪው መጽሀፍ በክፍል አምስት ከቃላት ትምህርት ይዘት ጋር ቦታ በመለዋወጥ መቀመጡን በመግለጽ እግረ መንገዳቸውን የአደረጃጀት መፋለስ ወይም አለመጣጣም እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

**ጥያቄ ሶስት፡-**በትምህርት መሳሪያዎቹ ከቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ወይም ይዘቶች መካከል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ፣ከጠባብ ወደሰፊ ወዘተ… አካሄድ ተከትለው የተደራጁ ይመስልዎታል? ካልሆነ ለምን?

**"ሀ"** "ከቅደም ተከተለዊ አደረጃጀት አንጻር የጎላ ክፍተት አለየሁም፡፡ የአንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች በተደጋገሚ መቅረብ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ለይዘቱ የሰጠውን የተለየ ትኩረት የሚያመለክት ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ግን በኋለኞቹ ምዕራፎች ስለ አረፍተነገር አመሰራረት የቀረበ ሀሳብ አለ፡፡ ይህ ይዘት ለክፍሉ ደረጃ ተገቢ መሆኑን ባላምንም መቅረብም ካለበት መቅረብ ያለበት በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች መሆን ነበረበት፡፡ ከጠባብ ወደ ሰፊ የሚለውን የመማር ማስተማር መርህ የሚያፋልስ ይመስለኛል፡፡"

**"ለ"** "የትምህርት መሳሪያዎቹ ለጽህፈት ክሂል ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች የሰጡት ትኩረት ከከዚህ ቀደሞቹ ጋር ሲነጻጸር መሻሻል የተየበት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሰፊ ክፍተት አላየሁበትም፡፡ ሆኖም ግን የይዘቶቹን ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከጠባብ ወደ ሰፊ ወዘተ… መሄድ ያለበትን የአደረጃጀት ሂደት ስያይ አነስተኛ ክፍተት ያለ ይመስላል፡፡ሁለቱም የአጻጻፍ አይነቶች ቢሆኑም በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ድርሰት ስለመጻፍ ካነሳ በኋላ በመሃልና በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ስለአንቀጽና አረፍተ ነገር መጻፍ ቀርቧል፡፡ድርሰት በመርሀ ትምህርቱ የተተኮረበት ቢሆንም አረፍተ ነገርንና አንቀጽን ማስቀደም ነበረበት ሚል እምነት አለኝ፡፡"

**"ሐ"** "ከአደረጃጀት አንጻር ያየሁት የሰፋ ክፍተት የለም፡፡ እንዳየሁት ከሆነ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከጠባብ ወደ ሰፊ ወይም ከተራ ወደ ውስብስብ አካሄድ በጥንቃቄ ተከትሎ የተደራጀ ዝግጅት ነው የሚል አመለካከት አለኝ፡፡"

**"መ"** "የጽህፈት ትምህርት ሲታሰብ አላባውያኑ ቃላት፣ዐረፍተ ነገሮች፣አንቀጾች ወዘተ… በሚል ቅደም ተከተል መደራጀት የጽህፈት ሂደታዊው መርህ መከተል ያለበት ቅደም ተከተል ነው፡፡ ሆኖም የትምህርት መሳሪያዎቹ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት የጎላ ክፍተት

ባይታይበትም በመነሻ ምዕራፎች አካባቢ ድርሰትን አስቀድሞ አረፍተ ነገርና አንቀጽ መጻፍን ወደኋላ ማድረጉ የአደረጃጀት ክፍተት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡”

ከቀረቡት አራት መላሾች መካከል አንዱ መላሽ ማለትም (25%) የሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀት ምንም እንከን የሌለውና ተገቢ እንደሆነ ሲያስቀምጥ፣ የቀሩት ሶስት መላሾች (75%) ከዚህ ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም በትንሹ የተለየ እይታ አላቸው፡፡መምህራኑ፣የትምህርት መሳሪያዎቹ የጽህፈት ክሂልና ርዕሰጉዳዮች አደረጃጀት የጎላ ክፍተት እንደሌለው በመጠቆም ጥቂት ክፍተቶች እንዳሉ አሳይተዋል፡፡ ከክፍተቶቹ መካከል የይዘት ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ ወይም ደግሞ ከጠባብ ወደ ሰፊ እያደጉ መሄድ ሲገባቸው፣ ከላይ በክፍል 4፣1. ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ በሚያጠናክር መልኩ በትምህርት መሳሪያዎቹ የኋላ ምዕራፎች አካባቢ አረፍተ ነገርን ስለማዋቀር የቀረቡት ትምህርቶች መቅረቡ ለዚህ ክፍል የሚሆን ቢሆን እንኳን መቅረብ ያለበት በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ቢሆን ኖሮ የይዘት ቅደም ተከተላዊ አደረጃጀቱ ከጠባብ ወደ ሰፊ መደራጀት ይችል እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡

**ጥያቄ አራት**፡-በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተመርጠው ወይም ተዘጋጅተው የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ ከመመጠን አንጻር ሁሉም ተገቢ ናቸው ብለው ያምናሉ?

**”ሀ”** “አብዛኞቹ ዝግጅቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ ስለሚመጥኑ ተገቢ ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ሆኖም ቢያንስ ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ለጀመረ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የአረፍተ ነገር መዋቅር ትምህርት ማቅረብ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡በተጨማሪም የስርዓተ ነጥቦች ትምህርት ከአረፍተ ነገር መዋቅር አደረጃጀት ጋር አብሮ የሚጀምር በመሆኑ በተገቢነቱ ላይ እምነት የለኝም፡፡”

**“ለ”** “አዲሶቹ ይዘቶች ተገቢ ናቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ምዕራፎች ውስጥ የአረፍተ ነገርን መዋቅር ለማስተማር ተብለው የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ይመጥናሉ ብዬ አልቀበልም፡፡ ምክንያቱም እስከ ስምንተኛ ክፍል በትክክል ተምረው ወደ ዘጠነኛ ክፍል የመጡ ተማሪዎች የአረፍተነገር አወቃቀርና ክፍሎች ያጠናቅቃሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡”

“ሐ” “የአረፍተነገር አወቃቀርን የመሰለ ከተማሪው የክፍል ደረጃ በታች የሆነ ትምህርት ከመቅረቡ ውጪ ያሉት ይዘቶች ለክፍሉ ተገቢ ናቸው፡፡ የአረፍተነገር መዋቅር ግን በዚህ ክፍል ባይቀርብ ጥሩ ነበር፡፡”

**"መ"** "ስለ አረፍተ ነገሮች ተዋቃሪዎች የቀረበው ትምህርት ደረጃውን የጠበቀ አይደለም። የአረፍተነገር ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ከሶስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል መጠናቀቅ ያለበት ስለሆነ ለዘጠነኛ ክፍል ተገቢ ዝግጅት አይደለም ብዬ አምናለሁ።

ሁሉም በቃለ መጠይቁ የተሳተፉት መምህራን ከላይ በክፍል 4.1.ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ በሚደግፍና በሚስማማ መልኩ አብዛኞቹ ይዘቶች ለክፍል ደረጃው የተስማማ ትምህርት መያዛቸውን ጠቅሰዋል።ከመላሾቹ 75% ወይም ሶስት መምህራን (የአገላለጽ ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ) የአረፍተ ነገር መዋቅር ትምህርት ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ለጀመሩ ተማሪዎች ከረጅም ጊዜ የትምህርት ቆይታ በኋላ በዘጠነኛ ክፍል ወደ ኋላ ተመልሶ ማቅረቡ የተማሪውን የክፍል የማይመጥንና ተገቢ ያልሆነ መሆኑን ገልጸዋል።ከመላሽ መምህራን መካከላ አንዱ መምህር (25%)ሌሎቹ መምህራን የሰጡትን መልስ ሙሉ በሙሉ በመድገም ከሌሎቹ በተላይ ደግሞ የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ትምህርትም በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ መቅረብ የሌለበት እንደሆነ ሲገለጽ ምክንያት ብሎ ያቀረበው ሀሳብ አረፍተ ነገር ማዋቀር የሚጀምር ተማሪ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጠቀምንም አንድ ላይ የሚያስኬድ ስለሆነ ስርዓተ ነጥቦችን በዚህ ክፍል ደረጃ በትምህርትነት የማቅረቡ ተገቢነት አሳማኝ እንዳልሆነ ገልጿል።

**ጥያቄ አምስት፡-** በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መጽሀፍ በጽህፈት ክሂል ይዘትነት ተዘጋጅተው የቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮችና መልመጃዎች በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ ከቅደም ተከተላዊ ትይዩነትና በመርሀ ትምህርቱ የቀረበው ርዕሰጉዳይ በተማሪው መጽሀፍ መልመጃ ወይም ይዘት ሆኖ ከመዘጋጀት አንጻር ተመሳሳይ ሆነው ነው የቀረቡት? ለምሳሌ በመርሀ ትምህርቱ ምዕራፍ አንድ፣ክፍል አንድ ድርሰት መጻፍ ከቀረበ፣ በተማሪው መጽሀፍም በትይዩ በምዕራፍ አንድ፣ክፍል አንድ ድርሰት መጻፍን የሚመለከት መልመጃ ቀርቧል?

**"ሀ"** "ሁሉቱንም የትምህርት መሳሪያዎች እያስተያየሁ ስያነብ ትይዩ ሆኖ የመቅረብ ችግር ብዙ ባይሆንም ያለ ይመስለኛል። ለምሳሌ የተማሪው መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት አንቀጽ የመጻፍ መልመጃ ሲያቀርብ፣መርሀ ትምህርቱ ግን "ገላጭ ድርሰት መጻፍ" የሚል ርዕስ አቅርቧል። በምዕራፍ ስድስትም የተማሪው መጽሀፍ ድርሰት የመጻፍ መልመጃ ሲያቀርብ፣በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበው ግን "አንቀጽ መጻፍ" የሚል ርዕሰ ጉዳይ ነው። እንዲሁ በሌሎች ምዕራፎችም በመርሀ ትምህርቱ "አንቀጽ ጻፉ" ወይም "ድርሰት ጻፉ" በሚል በግልጽ ርዕሰ ጉዳዩ ከቀረበ በኋላ በተማሪው መጽሐፍ ግን "በጽሁፍ ግለጹ" ወይም "ጻፉ" በሚልና ለተማሪው አሻሚ በሚመስል ትዕዛዝ የቀረቡ አሉ።"

**"ለ"** "በትምህርት መሳሪያዎቹ መካከል አንዳንድ ቦታ በአንዱ አንቀጽ በሚል የቀረበውን ሌላው ድርሰት ብሎ ማቅረብ አለ።በአንዳንድ ምዕራፎች ድርሰት መጻፍ በሚል የቀረበ ቢሆንም የድርሰቱ አይነት ያለመገለጽ ችግር አለ።በአንዳንድ ምዕራፎች የሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች ያለመናበብ በግልጽ ይታያል። ለምሳሌ በምዕራፍ አምስት መርሀ ትምህርቱ "ገላጭ ድርሰት መጻፍ" ብሎ ያቀረበው ርዕሰ ጉዳይ በመልመጃ ሲደገፍ በተማሪው መጽሀፍ "በጽሁፍ ግለጹ" ተብሎ ቀርቧል። ሆኖም ወደ ስህተት የሚመራ አይነት የተጣጣሚነት ችግር አላየሁበትም።"

**"ሐ"** "በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል የጽህፈት ክሂልን በሚመለከት የጎላ የተጣጣሚነት ችግር ያለ አይመስለኝም።"

**"መ"** "በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ባጠቃላይ በቃላት ጀምረው እስከ ድርሰት መጻፍ የዘለቁ ናቸው። ምናልባትም አንዱ ድርሰት ብሎ ያቀረበውን ሌላው አንቀጽ ብሎ ከማቅረብና መርሀ ትምህርቱ ያቀረበውን ርዕሰ ጉዳይ የተማሪው መጽሀፍ በሌላ ተቀራራቢ መልመጃ ከመተካት እንዲሁም በመርሀ ትምህርቱ ያልቀረበን ይዘት የተማሪው መጽሀፍ ከማቅረብ ባለፈ የከፋ የተጣጣሚነት ችግር በዝግጅቱ አላየሁም።"

ለጥያቄ አምስት አራቱም መላሾች ሶስት ተቀራራቢነት ያላቸውን መልሶች ሰጥተዋል።አንዱ መምህር (25%) በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ያለመጣጣም (ያለመናበብ) ችግር የለም የሚል ጠቅለል ያለ መልስ ሰጥቷል።ሌላዋ መምህርት (25%) አብዛኞቹ ይዘቶች ተናበው የቀረቡ እንደሆኑ በመናገር አንዳንድ ይዘቶች ግን በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ርዕሰ ጉዳይ ሆነው ሳይቀርቡ በተማሪው መጽሐፍ መልመጃ ሆነው እንደቀረቡ መረጃ በመጥቀስ ለማቅረብ ሞክረዋል።ሆኖም የመምህርቷ ምላሽ ችግር ያለበት ይመስላል።መርሀ ትምህርት ጽህፈት ብሎ ያላቀረበ እስካልሆነ ድረስ የመርሀ ትምህርቱ ጽህፈት በተማሪው መጽሐፍ አረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ድርሰት …የመሆን እድሉ ሰፊ ስለሆነ የግድ ድርሰት ወይም አንቀጽ ይባል የሚል አስገዳጅ ምክንያት አይኖርም።የቀሩት ሁለት (50%) መምህራን ምናልባት ከመርሀ ትምህርትና ከተማሪው መጽሀፍ የትምህርት ዝግጅት የሚያዘጋጅ ጀማሪ መምህርን ሊያደናግሩ የሚችሉ ጥቂት ያለመጣጣሞች ያሉ ቢመስልም አማዘኙ የጽህፈት ክሂል ትምህርት በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች የተጣጣመ እንደሆነ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል።ክፍተት ብለው የለዩዋቸው በመርሀ ትምህርቱ "ድርሰት መጻፍ" በሚል የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ በተማሪው መጽሐፍ በተወሰኑ ምዕራፎች "አንቀጽ መጻፍ" ሆኖ እንደቀረበና ይህ ጉዳይ ቦታ የመለዋወጥ ሁኔታ የታየበት ምዕራፍ እንዳለም ለማሳየት ሞክረዋል።በደፈናው አይነቱ ሳይገለጽ "ድርሰት ጻፉ" ብሎ በአንዱ ሲያቀርብ በሌላው አይነቱ የተገለጸበት ሂደት እንዳለም ጠቁመዋል።ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ አሻሚ ብለው በተላይ የተማሪውን መጽሀፍ ዋቤ በመድረግ ያቀረቧቸው

“ጻፉ” ወይም “በጽሁፍ ግለጹ” የሚሉ መልመጃዎች ሁለት ግልጽ ማድረጊያ አማራጮች አሏቸው፡፡አንደኛው ወደ መርሀ ትምህርቱ በመመለስ መርሀ ትምህርቱ “ጻፍ” የሚለው ምንን እንደሆነ ማየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሚጻፈው ነገር አንቀጽ ይሁን ድርሰት የቀረበውን የሀሳብ ስፋት በማየት መምህሩ የሚወስነው ይሆናል፡፡ነጠላ ሀሳብ ከሆነ አንቀጽ፣ ንኡሳን ሀሳቦች ያሉት ርዕሰ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ድርሰት ማድረግ ይቻላል፡፡

**ጥያቄ ስድስት** ፡-በአጠቃላይ የመርሀ ትምህርቱንና የተማሪውን መጽሀፍ መጣጣም በሚመለከት ያዩት ችግር ወይም የሚሉት ነገር ካለ ቢገልጹ፡፡

**“ሀ”** “በመሰረቱ በዘጠነኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ የመጨረሻ ገጾች የቀረበው የትምህርት መሳሪያ መርሀ ትምህርት ተብሎ መጻፍ ሲገባው ስርዓተ ትምህርት ተብሎ ቀርቧል፡፡ ይህም የዚህ ዝግጅት የጎላ ስህተት ሳይሆን አይቀርም፡፡ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ተደጋጋፊ ቢሆኑም ግለወጥ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ መስተካከል ያለበት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

**“ለ”** “መርሀ ትምህርት መባል የነበረበት ዝግጅት በዘጠነኛ ክፍል ስርዓተ ትምህርት ሆኖ መቅረቡ ግራ አጋብቶኝ የአስረኛን ክፍል ዝግጅት ለማየት ተገደድኩ፡፡ የአስረኛ ክፍል ተመሳሳይ ዝግጅት መርሀ ትምህርት ሆኖ መቅረቡ የዘጠነኛ ክፍሉ ስርዓተ ትምህርት ስህተት መሆኑን ተረዳሁ፡፡የዚህ ዝግጅት ጉልህ ስህተትም ይኸው ነው፡፡

**“ሐ”** “እስካየሁት ድረስ ዝግጅቱ ከቀድሞው ጋር ሲነጻጸር ጥሩ ዝግጅት ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የሚለው ነገር የለኝም፡፡

**“መ”** “እስካሁን ጥያቄው ስላልቀረበልኝ ጠበቅሁ እንጂ ከዘጠነኛ ክፍል የትምህርት መሳሪያዎች መካከል መርሀ ትምህርት መባል የነበረበትና ከመምህሩ መምሪያ ጋር ባንድ ጥራዝ ውስጥ የሚገኘው የትምህርት መሳሪያ ስርዓተ ትምህርት ተብሏል፡፡ ይህ ስህተት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ስር ስርዓተ ትምህርት፣ መርሀ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ በሚል ተለይተው የሚታወቁ የትምህርት መሳሪያዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ከስርዓተ ትምህርት ውጪ ሌሎቹ በመምህር እጅ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዝግጅት ስርዓተ ትምህርት ተብሎ በስህተት የቀረበው መርሀ ትምህርት ተብሎ መስተካከል አለበት የሚል አመለካከት አለኝ፡፡

ለዚህ ጥያቄ ሶስት ተቀራራቢ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡አንድ መምህር (25%) አዲሶቹ የትምህርት መሳሪያዎች ከቀድሞዎቹ ጋር ሲነጻጸር ተጣጣሚነታቸው የጎላ እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ ሌሎቹ ሁለት መምህራን (50%) ደግሞ መርሀ ትምህርቱን ለማንበብ ከመምህሩ መምሪያ ሲፈልጉ “ስርዓተ ትምህርት” ተብሎ መቀመጡ ግራ እንዳጋባቸው በመግለጽ

በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት መሰረት “መርሀ ትምህርት” ተብሎ መስተካከል እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ የቀረው አንድ መምህር (25%) ከቀሩት መምህራን የሰፋ ምልከታ በማድረግ አዲሶቹ የዘጠነኛ ክፍል የቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች ለጽህፈት ክሂል ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው እንደተዘጋጁ በመግለጽ በተለይ መርሀ ትምህርቱ ለድርሰት ትምህርት ልዩ አጽንኦት መስጠቱን በመረጃ አስደግፎ አሳይቷል፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ከቀረቡት 17 የጽህፈት ርዕሰጉዳዮች መካከል ሶስቱ አንቀጽ፣ ሰባቱ ድርሰት፣ በድምሩ አስር ርዕሶች ማለትም 62.5% ድርሰት ወይም ድርሰት ነክ መሆናቸው ሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ለጽህፈት ከሰጡት ትኩረት አንጻር ጉልህ የተጣጣሚነት ችግር እንደሌለባቸው ጠቁሟል፡፡

ባጠቃላይ የመምህራን ቃለመጠይቅ ትንታኔ የሚያሳየው በአዲሱ የ9ኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና በክፍሉ የተማሪ መጽሀፍ መካከል የጎላና ተግባቦትን የሚያደበዝዝ አይነት የርዕሰ ጉዳይና የይዘት ያለመጣጣም እንደሌለ ነው፡፡ሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ባሁኑ ወቅት አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩበት ያለው የጽህፈት ክሂል ትምህርት በተለይ ለአንቀጽና ለድርሰት ከፍተኛውን ድርሻ በመስጠት እንደተዘጋጀ አሳይተዋል፡፡ አንቀጽና ድርሰት ከጠቅላላ የጽህፈት ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ (62.5%) ሽፍነው መዘጋጀታቸው ተማሪዎች ጽህፈትን በስፋት እንዲለማመዱ የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከቃለመጠይቁ እንደአጠቃላይ ክፍተት ከቀረቡት ሀሳቦች የመጀመሪያው መርሀ ትምህርቱ ስርዓተ ትምህርት ተብሎ መቀመጡ ነው፡፡ ሁለተኛው የጽህፈት ክሂል በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች በተለያየ ክፍል የተቀመጠ ስለሆነ በተማሪው መጽሐፍ ከክፍል አምስት ወደ ክፍል አራት ቢመለስ የሚል የመምህራን አስተያየት የተሰጠበት፣ሶስተኛው የድርሰቱ አይነት ሳይጠቀስ በደፈናው “ድርሰት ጻፉ” የሚሉ የተማሪው መጽሀፍ ትዕዛዞችና “በጽሁፍ ግለጹ” በሚል የቀረቡት መልመጃዎች የሚጻፈውን ነገር በተለይ ለአዲስ መምህራን አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል ገልጾ ሊቀርብ በሚችልበት ሁኔታ ቢሻሻል የሚሉ አሰተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

በዚህ ጥናት በ2014 ዓ.ም.በአዲሱ የኢትዮጵያ ስርዓተ ትምህርት መሰረት ታትመው በ2015ዓ.ም. ለሙከራ ትግበራ በጥቂት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተሰራባቸው ባሉ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትና የተማሪው መጽሐፍ የጽሕፈት ክሂል ርዕሰ ጉዳይ፣ይዘትና መልመጃዎች ተገቢነት፣ አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ መጠናከርና መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ተደርሶበታል፡፡

በዚህ መሰረት አዲሶቹ የትምህርት መሳሪያዎች ባጠቃላይ፣ መርሀ ትምህርቱ በተለይ ለጽህፈት ክሂል ትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠታቸውን ለአንቀጽና ለድርሰት ትምህርቶች መርሀ ትምህርቱ ከ62% በላይ የይዘት ሽፋን መስጠቱ ይጠቁማል፡፡ይህ እይታ በክፍል ውስጥ ትግበራ

ከታከለበት አሁን እየታየ ያለውን ደካማ የጽህፈት አፈጻጸም ሊያሻሽለው እንደሚችል ይታመናል፡፡

ጥናቱ በድክመት የደረሰባቸው የተገቢነት፣ የአደረጃጀት ቅደምተከተል መዛባት፣የርዕስና የይዘት አቀራረብ ተጣጣሚነት ክፍተቶች ወዘተ…የትምህርት መሳሪያዎቹ ለሙሉ ትግበራ ዝግጅት ሲሻሻሉ የትኩረት ነጥብ ቢሆኑ የመግቢያችን የምሁራን ሀሳብ እንደሚጠቁመው በመጻህፍት ዝግጅት ወቅት የሚከሰቱ ስህተቶች ሊያስከትሉ የሚችሉትን የጽህፈት ክሂል ደካማ አፈጻጸም ማሻሻል ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ የጥናቱ ግኝትና የመፍትሔ ሀሳቦች

### 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ጅምር ላይ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት የነበረው ባሁኑ ወቅት በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመማር ላይ ባሉት ተማሪዎች ዘንድ የሚታየው ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ለዚህ ችግር መንስኤ ከሆኑት መካከል፣በትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ወቅት በትምህርት መሳሪያዎቹ ላይ የሚፈጠሩ ስህተቶች እንደሚገኙበት አለም (1992) ፣ ባየ (1987) እና ተስፋዬ (1981) ገልጸዋል፡፡

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በ2014 ተዘጋጅተው በ2015 ዓ ም በጥቂት የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙካራ ተግበራ ስራ ውስጥ በገቡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መርሀ ትምህርት ይዘቶችና ለዚሁ ክፍል በተዘጋጀው የተማሪ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ካሉት ይዘቶች መካከል በመጻፍ ክሂል ይዘት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በሁለቱም የትምህርት መሣሪያዎች መካከል ያለውን የመጻፍ ክሂል ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ተጣጥሞሽ ፈትሿል፡፡ ጥናቱ ከሰነድ ምርመራና ለጥቂት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል አማርኛ መምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ ተችቷል፡፡ መረጃውን በመተንተን ጥናቱ መታረም የሚገባቸውን ክፍተቶችና ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸውን ጥንካሬዎች ያሳየ ውጤት ተገኝቶበታል፡፡

### 5.2. የትናቱ ግኝት

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ከመርሀ ትምህርቱ ርዕሶች ጋር ያለውን መጣጣም መፈተሽ ነው፡፡ የይዘቶቹን አደረጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ አብዛኞቹ ይዘቶች የተማሪውን የቀደመ ዕውቀት መሰረት ያደረጉ፣የተከታታይነት የተለጣጣቂነትና የውህደት መርህን በመከተል ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተራ ወደ ውስብስብ አካሄድ ተከትለው የተደራጁ መሆኑ የትምህርት መሳሪያዎቹ ጠንካራ ጎን ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ሌላው በጥንካሬው የተገመገመው፣ አብዛኞቹ የጽህፈት ይዘቶች ተማሪዎቹ ተግባራዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚጋብዙ፣ የሚያሰሩና ተማሪዎች ሀሳብ አመንጭተው እንዲጽፉ የሚጠይቁ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሊጠናከሩ የሚገባ ሆኖ ጥናቱ በክፍተትነት የፈተሻቸው ግኝቶችም አሉ፡፡ እነዚህም፡-

•ለአንድ መምህር በእጁ ልገኙ የሚገባቸው የትምህርት መሳሪያዎች መርሀ ትምህርት፣ የመምህር መምሪያና የተማሪው መጽሀፍ ናቸው፡፡ ሆኖም አዲሱ የዘጠነኛ ክፍል ዝግጅት በመምህሩ መምሪያ መጨረሻ ገጾች አካባቢ መገኘት ያለበትን መርሀ ትምህርት፣ ስርዓተ ትምህርት ብሎ ነው ያቀረበው፡፡ መሆን ያለበት ግን መርሀ ትምህርት ነው፡፡ ለአስረኛ ክፍል በተዘጋጀው ተመሳሳይ ዝግጅት ግን መርሀ ትምህርት ተብሎ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለዚህ ይህ አንዱ የዝግጅቱ ደካማ ጎን ነው፡፡

•ይህ ጥናት አንድ ዋናና ሶስት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ከዝርዝር አላማዎቹ መካከል አንዱ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተደራጁት የጽሀፈት ክሂል መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በያዙት ቅደም ተከተል መቀመጣቸውን መገምገም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጽሀፈት ክሂል በመርሀ ትምህርቱ በክፍል አራት የተደራጀ ቢሆንም በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ግን በክፍል አምስት ተደራጅቷል፡፡የመጻፍ ክሂል ይዘት በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች በሁለት የተለያዩ የአቀራረብ ክፍሎች መገኘቱ የመጣጣም ክፍተት ነው፡፡

·በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተወሰኑ ምዕራፎች"ድርሰት ጻፉ"የሚል ትዕዛዝ ይሰጥና የሚጻፈው ድርሰት አይነት ለይቶ ያለማሳየት ችግር አለ፡፡ ·

•ሌላውና የጎላ ችግር ያመጣል ተብሎ የማያስጋ ቃል በቃል ትይዩ ቢሆን ተብሎ የሚታሰበው ክፍተት በመርሀ ትምህርቱ እና በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ መካከል ያለው የይዘት ቃል በቃል ያለመናበብ ችግር ነው፡፡በሁለቱም የትምህርት መሣሪያዎች በአንዱ ውስጥ የተጠቀሰው ይዘት በሌላው ያለመኖር፣ በሌላ ይዘት መቀየር ወይም ደግሞ የተሰጠው ይዘትና አድርጉ ተብሎ የቀረበው ትዕዛዝ የተለየ መሆን ናቸው፡፡ለምሳሌ በመርሀ ትምህርቱ ድርሰት መጻፍ በሚል ለቀረበው፣በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንቀጽ መጻፍ የሚል ትዕዛዝ ይቀርብለታል፡፡በመሳሪያዎቹ ውስጥ ካሉት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ አራት ውስጥ ያለው ይዘት ብቻ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ከመሆኑ ወጪ በሌሎቹ ምዕራፎች የጽሀፈት ትምህርት ሂደቱን በጎላ መልኩ ባያደበዝዙም ቃል በቃል የይዘት ያለመጣጣም ክፍተት የታየ መሆኑን ጥናቱ ለይቷል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሀሳቦች

የትምህርትን ስራ ስኬታማ ለማድረግ በየጊዜው የሚዘጋጁት የትምህርት መሳሪያዎች በዝግጅት ወቅትም ሆነ አገልግሎት እየሰጡ ባሉበት ጥንካሬያቸው እንዲጎለብትና ድክመታቸው እንዲሻሻል መፈተሽና ማጥናት ከትምህርት ባለሙያዎች የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

በዚህ መሰረት በ2014 ዓ ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በ2015 ዓ ም እየተሞከሩ በሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍ ጥናቱ ያገኛቸው ከሙሉ ትግበራ በፊት ሊሻሻሉ የሚገባቸውና ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው የጥናቱ ግኝት የሆኑ ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

•የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከአደረጃጀት አንጻር ውስን ክፍተቶች ቢኖሩም የተከታታይነትንና የተለጣጣቂነት መርሆችን ተከትለው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአረፍተ ነገር ወደ አንቀጽ ብሎም ወደ ድርሰት እያደገ የሄደ ዝግጅት ስለሆነ ለሙሉ ትግበራው ተጠናክሮ ቢቀጥል፣

•ከተገቢነት አንጻር በትምህርት መሳሪያዎቹ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በተላይም የአንቀጽና ድርሰት ይዘቶች ከጥቂት ክፍተቶች በቀር እንደ አጠቃላይ ሲታይ በሁለቱም ተሟልተው ስለሚገኙ የተጣጣሚነት ማሻሻያ ተደርጎባቸው ቢቀጥሉ፣

•የመምህሩ መምሪያ የመጨረሻ ገጾች ተጽፎ የሚገኘው የትምህርት መሣሪያ “መርሀ ትምህርት” ተብሎ መቅረብ ሲገባው “ስርዓተ ትምህርት” ተብሎ ቀርቧል፡፡ ስህተቱ ሀገራችን ከምትከተለው የትምህርት ስርኣት አንጻር ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ቢስተካከል፣

•በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መጽሀፍ ለዓመት የታቀደው ትምህርት በአስር አስር ምዕራፎች፣ እያንዳንዱ ምዕራፍ በስድስት በስድስት ክፍሎች፣ ስድስቱ ክፍሎች ደግሞ ክፍል1 ማዳመጥ፣ ክፍል2 ንግግር፣ ክፍል3 ንባብ፣ ክፍል4 ጽህፈት፣ ክፍል5 ቃላትና ክፍል6 ሰዋሰው በተባሉ ይዘቶች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ይሁን እንጂ የጽህፈት ክሂል በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአራተኛው ክፍል የተቀመጠ ሲሆን በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ደግሞ በክፍል አምስት እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ይህ የተፋለሰ አቀማመጥ የትምህርት መሣሪያዎቹ ለሙሉ ትግበራ ሲዘጋጁ የጽህፈት ክሂል ይዘት በሁለቱም ትምህርት መሳርያዎች በተመሳሳይ ክፍል ቢቀመጥ፣

•በየምዕራፉ በመርሀ ትምህርቱ የተጠቀመው ይዘት በመማሪያ መጽሀፉ ያንኑ ይዘት በሚያስተምሩ መልመጃዎች መጠናከር ነበረበት፡፡ ይሁን እንጂ ከአስሩ ምዕራፎች መካከል በመርሀ ትምህርትና በመማሪያ መጽሀፍ ፍጹም ተመሳሳይ ይዘት ”ዘገባ መጻፍ” የተገኘው በምዕራፍ አራት ብቻ ነው፡፡በሌሎቹ ምዕራፎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበው ይዘት አንድ ሆኖ በመማሪያ መጽሀፉ የቀረበው ደግሞ ሌላ ነው፡፡ ሁኔታው ጠቅለል ሲደረግም በዘጠኙ ምዕራፎች በመርሀ ትምህረትና በመማሪያ መጽሀፍ የቀረቡት ይዘቶች በመጠንም ሆነ በአይነት ትይዩ ወይም ተመጣጣኝ ሆነው አልቀረቡም፡፡ይህም በሁለቱ የትምህርት መሳሪያዎች

መካከል የጽህፈት ክሂል ይዘት አቀራረብን በተመለከተ የተጣጥሞሽ ችግር መኖሩን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የትምህርት መሳርያዎቹ ለሙሉ ትግበራ ሲሻሻሉ እነዚህ ክፍተቶች እርምት እንዲያገኙ ቢደረግ የሚል የመፍትሔ ሀሳብ በመስጠት አጥኚው ጥናቱን አጠናቋል፡፡

# ዋቤ መጻህፍት


ማረው አለሙ፡፡ (1996)፡፡ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው፡፡አዲስ አበባ፣ት.መ.ማ.ማ.ድ.

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡ ስነ ልሳን እና ቋንቋን ማስተማር (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡(2014)፡፡ አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ የተማሪው መጽሀፍ ዘጠነኛ ክፍል

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡(2014)፡፡ አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ የመምህር መምሪያ ዘጠነኛ ክፍል

ንገሡ ደሳለኝ ፡፡(1998)፡፡የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና ለክፍል ደረጃው በ1991ዓ ም በተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ መካከል ያለው ተጣጥሞሽ፣ ለድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ፡፡

አለም እሼቱ፡፡(1992)፡፡መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አማረ ተሾመ፡፡ (2010)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ፡፡(በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙካራዊ ጥናት)፡፡

አሰቴር ግርማ፡፡(2007)፡፡ በ2001ዓ ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሸሽለው በተዘጋጁት የ11ኛና የ12ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶችና በመማሪያ መጻህፍት መካከል የለው የይዘት ዝምድና፣ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡(2009)፡፡የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡(1996) ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ጽጌ ታፈሰ፡፡(1992)፡፡ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል? አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፡፡

Ariningsih, (2010). The effectiveness of using picture series to improve the student writing skill viewed from their learninc motivation.Thesis submitted for graduate in English. Education, Sehelas maret University

Attkine J.and et Al.(1996) skills development methodology.Addis Ababa University press.

Byme. D (1988).Teaching writing skills, longman;longman group UK Lmi.

Byme.(1997). Teaching writing skills. London; longman Group Ltd

Cunnings worth,A.(1984).Evaluting and selecting EFL Teaching material London;

Heinemann.Educational Books.

---------------(1995).Choosing your course book. Oxford; Heinemann.

Dubin,F and E olishtain (1996) course design development program andmterial for language

learning,Cambridge.

Dyer,B.(1996) Lx and L2 composition Theories HIlloks Environmental mode task based

longuote teaching ELT journal 50/41,pp,312-317

Flower, L. and Hayes, J. R.(1981)A Cognitive pross theory of writing.College composition and

communication,Vol,32,365-387.

Grant, N. (1987). Making the most of your text book. London; Longman.

Harmer, J. (1991). The practice of English language teaching.london,longman.

Harmer, J. (1993) Introducing Writing. London; Penguine.

Hedge, T. (1988) Writing. Oxford, Oxford university press.

McDonough,J and C. show,(1993) material and methods in ELT:Ateachers guide
Oxford black Nell Publishers.

Murry, D.M. Learning by teaching Selected Articles on Writing and teaching.
London; Heinemann

Nunan, D.(1988). Syllabus designs. Oxford; Oxford University press.

-------------(1989). Designing Tasks for the communicative classroom.cambridge.
Cambride university press.

-------------.(1991) Language Teaching Methodology .A text Book for Teachers.
Oxford; International Book distribution Ltd.

Parks J and harrs, M, B.(2002) The purpose of a Syllabus.CBSCO publishing
Vol.50/ No 2

Pincas, A.(1982). Teaching English Writing. London: Macmillan Pulishers Ltd

Raimes, A.(1983) Techaniques in teaching writing.Oxford university press.

Richards J. C.(1974) Error Anairsis perspectives on second language acquisition.
London and Newyork. Longman group Ltd.

---------------(1987). The context of language Teaching ;Cambridge.Cambridge
Uhiversity Press.

---------------(1990). The Language teaching matrix. Cambridge; Cambridge
University Press.

Richards, J. C.& Rodgers, T.S. (1986) Approaches And Methods in language
Teaching. Cambridge; Cambridge University press.

Tayler.(1949). Basic principles of curriculum and instruction.Chicago; Chicago

University press

Ur,p. (1996). A Course in lahguage Teaching. Practice and Theory. Cambridge; Cambridge

University press.

------------(2006) ACourse in language Teaching Practice and Theory.Cambridge

Cambridge university press.

Widdowson, H. G. (1978) Teaching Language as Communication. Oxford: oup.

Yalden, J. (1987). Principles of Course design for language teaching.Cambridge

Cambridge University Press.

**ድረ ገጾች**

https// advising.stanford.edu.

https//shore light.com

# አባሪ

## ለመምህራን ቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

ውድ መምህር/ርት፣ ጊዜዎትን ሰውተው፣ የ9ኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ አንብበው ስለጠበቁኝና ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ። በመቀጠል የምጠይቅዎት ጥያቄዎች ለጥናቴ መረጃ ከመሆን የዘለለ ሌላ ምንም አላማ የሌላቸው ስለሆነ በነጻነት ምላሽ እንዲሰጡኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

1/ስምዎትን ብነግሩኝ?

2/ በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ምን ያህል አገለገሉ?

3/ ከቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች መካከል መርሀ ትምህርት አንዱ ሲሆን በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ስፋት አግኝተው በይዘትነት የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮችን ይጠቁማል። እርስዎ መርሀ ትምህርትን እንደ ትምህርት መሳሪያ የሚጠቀሙት መቼ መቼ ነው?

4/ አዲስ በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች በክሂልና ዕውቀት ዘርፎች ሲከፋፈሉ የአከፋፈል ሂደቱ ክፍል አንድ፣ሁለት፣ሶስት፣አራት፣አምስትና ስድስት በሚሉ ክፍሎች ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳና የመማር ሂደታዊ ቅደም ተከተል ይዘው እንደተዘጋጁ በተማሪው መጽሀፍ መግቢያ ላይ ተገልጿል። ይህ ቅደም ተከተል በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ የተባለውን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል ጠብቀው ተዘጋጅተዋል?

5/ በትምህርት መሳሪያዎቹ ከቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ወይም ይዘቶች መካከል የጽህፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ፣ከጠባብ ወደሰፊ፣ ወዘተ... አካሄድ ተከትለው የተደራጁ ይመስልዎታል? ካልሆነ ለምን?

6/ በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተመርጠው ወይም ተዘጋጅተው የቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮችና ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ ከመመጠን አንጻር ሁሉም ተገቢ ናቸው ብለው ያምናሉ?

7/በመርሀ ትምህርቱና በተማሪው መጽሀፍ በጽህፈት ክሂል ይዘትነት ተዘጋጅተው የቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮችና መልመጃዎች፣በሁለቱም የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ ከቅደም ተከተላዊ ትይዩነትና በመርሀ ትምህርቱ የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ በተማሪው መጽሀፍ መልመጃ ወይም ይዘት ሆኖ ከመዘጋጀት አንጻር ተመሳሳይ ሆነው ነው የቀረቡት? ለምሳሌ በመርሀ ትምህርቱ ምዕራፍ አንድ፣ክፍል አንድ ድርሰት መጻፍ ከቀረበ፣ በተማሪው መጽሀፍም በትይዩ በምዕራፍ አንድ፣ክፍል አንድ ድርሰት መጻፍን የሚመለከት መልመጃ ቀርቧል?

8/በአጠቃላይ የመርሀ ትምህርቱንና የተማሪውን መጽሀፍ መጣጣም በሚመለከት ያዩት ችግር ወይም የሚሉት ነገር ካለ ቢገልጹ።

ስለ ትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ።